በመጨረሻ የቃሉ ቀለሞች /አ - ልእን -ንኧ - ግእግ -ግኧር -ንአች - ችኧውም/ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ ቃሉ ባለ ሰባት ቀለም ስለሆነ፣ ውስብስብ ነው፡፡ የአወቃቀሩ ስርዓት የአማርኛ ብቻ ሳይሆን፣ የማንኛውም ቋዋንቋዋ ነው፡. ስርዓቱን በትክክል ከተከተልን፡ የቱ ተናባቢ ከየቱ አናባቢ ጋር መዋቀር እንዳለበት በቀላሉ እንረዳለን፡፡ ሰባተኛው ቀለም ሁለት ጨራሺ ተናባቢዎች አሉት፡፡ ይሁን እንጅ ከነዚህ ተናባቢዎች ቀጥሎ አንድ አናባቢ ለምሳሌ፡ /እ/ ቢገባ፣ ከሁለቱ ጨራሺ ተናባቢዎች፡ የመጨረሻው፣ ማለትም /ም/፣ ከዚህ አናባቢ ጋር ይዋቀርና /ምእ/ የሚል ስምንተኛ ቀለም ይፈጥራል፡፡ ይህ ሲሆን፣ ሰባተኛው ቀለም አንድ ጨራሺ ተናባቢ ብቻ ይኖረዋል፡፡ በዚህ አካሄድ፣ የአማርኛ መደበኛ ወይም አይነተኛ የቀለም አወቃቀር፣ ከላይ በተራ ቁጥር (5) እንደሚታየው፣ /ተአተ/ የሚል ስርዓት እንደሚከተል ያሳያል፡፡

ከላይ በተዘረዘረው ሁኔታ የሚዋቀሩ ቀለሞች ዝግና ክፍት ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ዝግ የሚባሉት ጨራሽ ተናባቢ ያላቸው ሲሆኑ፣ ክፍት የሚባሉት ጨራሽ የሌላቸው ናቸው፡፡ ከላይ በተራ ቁጥር (6) ከተመለከቱት ሰባት ቀለሞች ውስጥ የመጀመሪያውና ሶስተኛው ብቻ ክፍት ናቸው፡፡

ፎኒሞች ከላይ በተዘረዘረው ሁኔታ ቀለምን ለመፍጠር ሲዋቀሩ ርስበርስ ከሚፈጥሩት ጉርብትና የተነሳ በራሳቸው ላይ የተለያዩ ለውጦች ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ለውጡን የሚያስከትሉት ድምፀ-ልሳናዊ ሂደቶች ይባላሉ፡፡ የለውጡን ዝርዝር ሁኔታ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## *ድምፀ ልሳናዊ ሂደት*

ከፍ ሲል ወደ ተነሳንበት የፎኒሞች ቅንጅት እንደገና እንመለስና በአቀነጃጀቱ ምክንያት ፎኒሞቹ ከሚፈጥሩት ጉርብትና የተነሳ በተቃናጅ ፎኒሞች ላይ ስለሚደርሰው ለውጥ እንወያይ፡፡ ከዚያ በፊት ግን ከሁለት ቃላት ጋር እንተዋወቅ፡፡ እነዚህም _ነዕነይ_ እና _ታህታይ_ የሚሉት ናቸው፡፡ በውይይታችን ላይ እየደጋገሙ ስለሚመጡ፣ ከወዲሁ ግልፅ ሊሆኑልን ይገባል፡፡ ላዕላይ ማለት እንደበታዊ፣ ማለትም ከአንደበት የሚወጣና በጆሮ የሚሰማ ማለት ነው፡፡ ታህታይ ደግሞ አዕምሮአዊ፣ ማለትም በአዕምሮአችን ብቻ የሚሰማንና የምናውቀው፣ ግን በአንደበታችን የማናወጣው፣ ማለት ነው፡፡ አዕምሮአዊ የሆነ ነገር ረቂቅ ሲሆን፣ አንበደበታዊ የሆነ ደግሞ ግዝፍ ነው፤ እንደ ምሳሰ ባለ ግዝፍ የአንደበት አካል ስለሚፈጠርና በጆሮም ስለሚሰማ፡፡ ፎኒሞች አዕምሮአዊ ስለዚህም ረቂቅ ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ አካላዊ፣ ማለትም እንደበታዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህም የሚሆነው በንግግር ጊዜ ከአዕምሮ ወጥተው በአንደበት አካላት አማካኝነት ሊፈጠሩ ወይም ሲገዘፉ ነው፡፡ እያንዳንዱ ፎኒም በአዕምሮ ውስጥ ረቂቅ የሆነ ገፅታ ሲኖረው፣ በአንደበት አማካኝነት በመካነ ፍጥረት ላይ በሚፈጠርበት ጊዜ አካላዊ የሆነ ገፅታ ይኖረዋል፡፡ በዚህም ምክንያት እያንዳንዱ ፎኒም ቢያንስ አንድ አካላዊ ገፅታ ይኖረዋል፡፡ ከዚህ ልዩነት በመነሳት፡

አዕምሮአዊ ገፅታውን ታህታይ፣ አካላዊ ገፅታውን ላዕላይ እያልን አንጠራዋለን፡፡ ይህ በፎኒም ብቻ ሳይሆን፣ ወደፊት እንደምናየው፣ በምዕላድ፣ በቃላት፣ በሀረጋትና በአረፍተ ነገር አወቃቀር ላይም የሚታይ አጠቃላይ የቋንቋዋ ባህሪ ነው[13]፡፡

ፎኒሞች ቀለማትን ለመመስረት ርስበርስ ሲቀናጁ የሚፈጥሩት ቅርፅ ታህታይ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ማንኛውም ፎኒም አንድ ቅርፅ ብቻ አለው፡፡ ይህ ቅርፅ ከአንደበት በሚወጣበት፣ ማለትም በንግግር ጊዜ በአንደበት አካላት ሲፈጠር፣ መልኩ በከፊል ወይም በሙሉ ሲለወጥ ይችላል፡፡ ስለዚህም ከአንድ በላይ የሆኑ አንደበታዊ (ላዕላይ) ቅርፆች ይኖሩታል፡፡ እነዚህም የተለያዩ ቅርፆች ዘረ ፎኒም እንደሚባሉ ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡ የለውጡ መንስዔ አንዱ ፎኒም ከሚቀድመው ወይም ከሚከተለው ሌላ ፎኒም ጋር የሚፈጥረው ጉርብትና እና ይህም የሚያስከትለው ንክኪ ብሎም የባህሪ መወራረስ ሂደት ነው፡፡ ሁለቱን ቅርፆች ለመለየት ላዕላዩን በቅንፍ፣ ታህታዩን በዕዝባር ውስጥ እንፅፈዋለን፡፡ የታህታዊው አፃፃፍ ፎኒማዊ ሲባል፣ የላዕላዊው ዘረ ፎኒማዊ ወይም ንበታዊ ይባላል፡፡ ይህንም ቀደም ሲል በመጠኑም ቢሆን አይተነዋል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ሁኔታውን <u>በርቺ</u> የሚለውን ቃል አንውሰድና እንደገና በምሳሌ እንረዳው፡፡ የቃሉ ስርዓተ ፅህፈታዊ ቅርፅ ያው <u>በርቺ</u> ነው፡፡ ላዕላይ ዘረ ፎኒማዊ ቅርፁ [ብኧርችኢ] ነው፡፡ ታህታይ ቅርፁ ግን /ብኧርትኢ/ ነው፡፡ ይህ በአዕምሮአችን የሚለማን ቅርፅ ነው፡፡ በሁለቱ ቅርፆች መካከል ያለው ልዩነት፣ በታህታዩ ቅርፁ ውስጥ /ት/ የነበረችው ተናባቢ የድድ ድምፅ በላዕላዩ ቅርፅ ወስጥ ወደ ድላንቃ ተለውጣ [ች] መሆንዋ ነው፡፡

እዚህ ላይ [ች] በታህታዩ ቅርፅ ውስጥ /ት/ ለመሆንዋ ማስረጃው ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ሲነሳ ይችላል፡፡ ድምፅዋ /ት/ ለመሆንዋ ማስረጃው፣ ለተባዕታይ ፆታ የምንጠቀምበት የቃሉ ቅርፅ ነው፡፡ እሱም በርታ [ብኧርትአ] ነው፡፡ ከ[ር] ቀጥሎ የምትታየው ድምፅ [ት] ነች፡፡ የቃሉ ታህታይ ቅርፅም /ብኧርትአ/ ነው፡፡ ከላዕላዩ ቅርፅ ጋር አንድ አይነት ነው፡፡ በ/ብኧርትአ/እና በ/ብኧርትኢ/ መካከል ያለው ልዩነት በመጨረሻዎቹ አናባቢዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም የ/ብኧርትኢ/ የመጨረሻ አናባቢ /ኢ/ ሲሆን፣ የ/ብኧርትአ/ የመጨረሻ አናባቢ /አ/ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በሁዋላ የሚነሳው ሌላው ጥያቄ /ብኧርትኢ/ በሚለው ታህታይ ቅርፅ ውስጥ /ት/ የነበረችው ፎኒም [ብኧርችኢ] በሚለው ላዕላይ ቅርፁ ውስጥ እንዴት ወደ [ች] ተለወጠች? ከተለወጠችስ <u>በርታ</u> በሚለው ላይ ለምን አልተለወጠችም የሚል ነው? ወደፊት ጉዳዩን በዝርዝር እስከምናየው ድረስ

---

[13] ባህሪነቱ ግን የቋንቋዋ ብቻ አይደለም፤ ማንኛውም ነገር ረቂቃዊና አካላዊ ባህሪ አለው፡፡ ለምሳሌ፣ የሰው ተፈጥሮ በከፊል አካላዊ (ሲጋዊ) በከፊል ደግሞ መንፈሳዊ (ረቂቅ) ነው፡፡ ነፍስና ስጋ እያልን አንዱን ከሌላው እንለያለን፡፡ ስጋ ተሰዋዋጭ ነው፣ ይከሳል፣ ይጠቁራል፣ ያድጋል፣ ይሟሟል፣ ይሞታል፣ ይበሰብሳል፡፡ ነፍስ ግን አትሰዋወጥም፣ አትሞትም፤ ዘላለማዊት ናት ይባላል፡፡

/ብኧርትኢ/ በሚለው ውስጥ /ት/ ወደ [ች] የምትለወጠው /ኢ/ ከሚለው አናባቢ በፊት ገብታ ስትገኝ ብቻ ነው ብለን፣ አናልፈዋለን፡፡

የሁለቱን ቃላት ቀለማዊ አወቃቀር በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡




ከዕፀ-መዋቅሩ እንደምናየው፣ ምዕላዱ ባለሁለት ቀለም ሊሆን፣ የመጀመሪያው ቀለም ዝግ ነው፡፡ በተናባቢ ይጨርሳል፡፡ ሁለተኛው ጨራሽ ተናባቢ ስለሌለው ክፍት ነው፡፡ ለውጡም የሚካሄደው በሁለተኛው ቀለም ከፋች ተናባቢ በሆነችው በ/ት/ ላይ ነው፡፡ መንስዔውም ከፍ ሲል እንደተገለፀው፡ ከጎንዋ የሚገኘው /ኢ/ የሚለው አናባቢ ነው፡፡ አሁን ወደ ርዕስ ጉዳያችን እንመለስና ሌሎች ድምፀ-ልሳናዊ ሂደቶችን እንመልከት፡፡

## ምስለት

ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ በአንድ ቅንጅት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ፎኒሞች በትንጅቱ ውስጥ በሚፈጥሩት ጉርብትና ምክንያት፣ የአንዱ ባህሪ ወደ ሌላው ሊጋባ ይችላል፡፡ በዚህም ተጋቦት ምክንያት አንዱ ሌላውን ሊመስል ይችላል፡፡ የመመሳሰሉን ሂደት ምስስሎሽ፣ ውጤቱን ደግሞ <u>ምስለት</u> እንለዋለን፡፡ አንድ ድምፅ ከጎረቤቱ ጋር ይመሳሰላል የምንለው የጎረቤቱን ድምፅ ባህሪ በከፊል ወይም በሙሉ ሲወስድና እሱን ሲመስል ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የምስሉቱን ሂደት ከፊል ወይም ሙሉ ምስስሎሽ እንለዋለን፡፡ አንድ ድምፅ ከጎረቤቱ ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሳሰሎአል የምንለው፣ ጎረቤቱ በሚፈጠርበት ቦታና ሁኔታ እሱም

ሲፈጠር ነው፡፡ ይህም ከጎረቤቱ ጋር በመካነ ፍጥረቱና በባህርየ ፍጥረቱ አንድ ሲሆን ነው፡፡ ከጎረቤቱ ጋር በከፊል የሚመሳሰለው፣ ከሁለቱ በአንዱ ብቻ ሲመሳሰል ነው፡፡

ሁለቱን ባህሪ ተወራራሽ ድምፆች መሳይና እለመሳይ እንላቸዋለን፡፡ መሳዩ ባህሪ ወሳጁ ሲሆን፣ እስመሳዩ ባህሪ ሰጭው ነው፡፡ መሳዩ ድምፅ ሁለት ቅርፅ ይኖረዋል፡፡ አንዱ የጎረቤቱን ባህሪ ከመውሰዱ በፊት የነበረው ሲሆን፣ ሁለተኛው ባህሪውን ከወሰደ በሁዋላ የሚያገኘው ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የመጀመሪያውን ታህታይ፣ ሁለተኛውን ላዕላይ ቅርፅ እንለዋለን፡፡ ለምሳሌ /ብእርትኢ/ በሚለው ውስጥ የምትታየው /ት/ የምትለዋ ፎኒም /ኢ/ የሚለውን የፊት አናባቢ ባህሪ ስትወስድ [ች] ትሆናለች፡፡ ስለዚህም ፎኒምዋ ሁለት ቅርፅ አላት፣ /ት/ እና [ች]፡፡ ከዚህ መንደርደሪያ አንፃር የተለያዩ የምስለት አይነቶችን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## ከናፍራዊነት

ከናፍራዊነት ከምስለት አይነቶች አንዱ ነው፡፡ የሚከሰተውም አንድ በመካነ ፍጥረቱ የከናፍር ያልሆነ ድምፅ ከናፍራዊ በሆነ ድምፅ ንክኪ ምክንያት ወደ ከናፍር ድምፅ ሲለወጥ ነው፡፡ ሁኔታውን በሚከተሉት ምሳሌዎች አናሳያለን፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| /እንብእሰስእ/ | [ አምብእስስእ] | አንበሳ | 1 |
| /አንብእጥጥእ/ | [ እምብእጥጥአ] | እንበጣ | |
| /ከእንፍእር/ | [ከእምፍእር][14] | ከንፈር | |

እነዚህ ቃላት እያንዳንዳቸው ሶስት ሶስት ጊዜ ተፅፈዋል፡፡ መጀመሪያ በእዝባር ውስጥ፣ ከዚያ በማዕዘን ቅንፍ ውስጥ፣ በመጨረሻ ደግሞ በመደበኛው የአፃፃፍ ስርዓት ተመዝግበዋል፡፡ በእዝባር ውስጥ የሚታየው ቅርፃቸው ፎኒማዊ፣ ማለትም እዕምሮአዊ ሲሆን፣ በማዕዘን ቅንፍ ውስጥ የሚታየው ዘረ ፎኒማዊ፣ ማለትም አንደበታዊ ወይም ንበታዊ ቅርፅ ነው፡፡ ፎኒማዊ ስንል ታህታይ፣ ዘረ ፎኒማዊ ስንል ላዕላይ ቅርፅ ማለታችንን እንርሳ፡፡ የታህታይና ላዕላይ ልዩነት ቀደም ሲል እንደተገለፀው ነው፡፡ ላዕላዩ የታህታዩ አንደበታዊ ክሳች ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በታህታዩ ውስጥ የሌለ ባህሪ ሲያሳይ ይችላል፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የሚታየው ስርዓተ ፅህፈታዊ፣ ማለትም ፊደላዊ ቅርፅ ነው፡፡ ይህ አፃፃፍ ከላዕላይም ሆነ ከታህታይ ቅርፅ ጋር ግንኙነት ላይኖረው ይችላል፡፡ መሰረቱም ስነ-ልሳናዊ ሳይሆን፣ ባህላዊ

---

[14] እዚህ ላይ [ም] የሚለው ድምፅ ሙሉ በሙሉ የከናፍር አይደለም፡፡ የታችኛው ከንፈር የላይኛውን የፊት ጥርስ ሲነካ የሚፈጠር ስለሆነ፣ የስነፈር (የጥርስና የከንፈር) ድምፅ ነው፡፡ በአለማቀፋዊው የስነ-ልሳን ፊደል ይህ ድምፅ የሚወከለው በ[ɱ] ነው ፡፡ የሙሉው ቃል ዘረ-ፎኒማዊ ቅርፅ በዚህ ፊደል ሲፃፍ [käɱfär] የሚል ይሆናል፡፡

ለውጥ፣ ማለትም ለልሣኔ ያመጣው የፅህፈት ጥበብና የአፃፃፍ ስርዓት ነው፡፡ ይህም እንደየስልጣኔው አይነት ይለያያል፡፡ ለምሳሌ፣ የአረብኛው አፃፃፍ ከእንግሊዝኛው፣ የፈረንሳይኛው ከቻይንኛው፣ ወዘተ፣ ይለያል፡፡

በዘረ ፎኒማዊው (ንበታዊ) ቅርፅና በፎኒማዊው ቅርፅ መካከል መጠነኛ ልዩነት ይታያል፡፡ ይኸውም በፎኒማዊው ቅርፅ /ን/ ሆና የምትታየው፣ በዘረ-ፎኒማዊው ቅርፅ [ም] መሆንዋ ነው፡፡ ጥያቄው ታድያ ይህ ለውጥ ከየት መጣ? የሚል ነው፡፡ ለዚህ በፎኒማዊው ቅርፅ ውስጥ የ/ን/ን አሰላለፍ እንደገና ማየት ያስፈልጋል፡፡ ይህች ፎኒም የገባችው ከ/ብ/ ቀድማ ነው፡፡ /ብ/ ደግሞ እግድ የከናፍር ድምፅ ነች፡፡ አየር በአፍ በኩል ሲያልፍ፣ ከናፍር ተጋጥመው ሲላቀቁ የምትፈጠር እግድ ድምፅ ነች፡፡ /ን/ ሰርናዊ የድድ ድምፅ ነች፡፡ አየር በሰርን በኩል ሲያልፍና የምላስ ጫፍ ድድን ሲነካ ትፈጠራለች፡፡ በሁለቱ ፎኒሞች መካከል ያለው ልዩነት የመካነ ፍጥረት፣ ማለትም የመፈጠሪያ ቦታ ብቻ ነው፡፡ ሁለቱም ነዛሪ ስለሆኑ፣ በባህርየ ፍጥረታቸው አንድ ናቸው፡፡ በላዕላይ ወይም ዘረ-ፎኒማዊ ቅርፅ ውስጥ /ን/ ወደ [ም] የተለወጠችው፣ በመካነ ፍጥረት ነው፡፡ የድድ የነበረችው ድምፅ የከናፍር ሆናለችና፡፡ ወደ ከናፍር ድምፅነት የተለወጠችውም፣ ከጎንዋ በሚገኘው የከናፍር ድምፅ፣ ማለትም በ/ብ/ ምክንያት ነው፡፡ የዚህ ድምፅ ከናፍራዊነት ወደ እሰዋ ተጋብቶአል፡፡ ስለዚህም /ን/ ወደ [ም] ተለወጠችና በመካነ ፍጥረትዋም /ብ/ን ልትመስል ቻለች፡፡

ምስስሎሹ ግን ከፊል ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ የባህርየ ፍጥረት ልዩነት በመካከላቸው አለ፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ሁለቱም ሰርናዊና ነዛሪ ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ፣ ከአየር አወጣጥ አንፃር፣ ሁለቱ ድምፆች አሁንም የተለያዩ ናቸው፡፡ /ብ/ እግድ ስትሆን፣ /ን/ ልቅ ነች፡፡ ስትፈጠር አየር ሳይታገድ በነፃ በሰርን በኩል እድርጎ ይወጣል፡፡ /ን/ ሙሉ በሙሉ /ብ/ን ብትመስል ኖሮ፣ ቅርፅዋ [ም] ሳይሆን [ብ] ይሆን ነበር፡፡ ስለዚህም [እምብኧለስእ] የነበረው ቃል [እብብኧስስአ] ይሆን ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ተቀባይነት ያለው ቃል አይደልም፡፡ ስለዚህም አይባልም፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ታህታዊው ቅርፅ አዕምሮአዊ ስለሆነ፣ ለላዕ-ላዊው ቅርፅ መሰረት ነው፡፡ ላዕላዩ የታህታዩ ልዋጭ ወይም ክሳች ነውና፡፡ ልዋጩና መሰረታዊው ድምፅ ያላቸውንም ዝምድና በ<u>*ቅምር*</u> ማሳየት ይቻላል፡፡ ቅምሩ እንድ ታህታይ ቅርፅ ወደ ላዕላይ ቅርፅ እንዴት እንደሚለወጥ የሚያሳይ ስለሆነ፣ <u>*ለዋጭ ህግ*</u> እንለዋለን፡፡ በዚሁ መሰረት ከፍ ሲል ያየነውን ለውጥ እንደሚከተለው እድርገን እናሳያለን፡፡

/ን/ ⟶ [ም] / - /ብ/ 2

ይህ ቅምር /ን/ ከ /ብ/ በፊት ስትገባ ወደ [ም] ትለወጣለች የሚል ነው፡፡ ይበል እንጅ፣ /ን/ ወደ [ም] የምትለወጠው ከ/ብ/ በፊት ብቻ ለትገኝ አይደለም፡፡ ለምሳሌ፣ [ከኧምፍኧር] የሚለው ቃል ታህታይ ቅርፅ /ከኧንፍኧር/ ነው፡፡ በዚህ

ባህሪን እንጅ ከዚህ ወይም ከዚያ ድምፅ በፊት አያለ ስለማይዘረዝር በተራ ቁጥር (3) ከተጠቀሰው ቅምር የበለጠ እጠቃልይነት አለው፡፡ ይህን ከተገነዘብን፣ ወደ ሌላ የምስለት አይነት እንሂድ፡፡

## ከፊል ላንቃዊነት

ይህ የምስለት አይነት በተናጠላዊ ፍጥረታቸው ላንቃዊ ያልሆኑ ድምፆች በቅንጅታዊ ባህሪያቸው ምክንያት ከፊል ላንቃዊ የሚሆኑበት ሂደት ነው፡፡ የሚከተሉት ለዚህ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ቃላት ናቸው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| /ክኢስ / | [ክʸኢስ] | ኪስ | I |
| /ብኤት/ | [ ብʸኤት] | ቤት | |
| /ጥኢስ/ | [ጥʸኢስ] | ጢስ | |
| /ምኸልትኢ/ | [ምኸልትʸኢ] | መልቲ | |
| /ክኸይስኢ/ | [ክኸይስʸኢ] | ክይሲ | |

የእነዚህ ቃላት ታህታይ ቅርፅ በእዝባር ውስጥ የተመለከተው ነው፡፡ ላዕላይ ቅርፃቸው በቅንፍ ውስጥ የሚታየው ነው፡፡ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት በታህታዩ ውስጥ /ክ፣ብ፣ጥ፣ት፣ስ/ የነበሩት ፎኒሞች በላዕላዩ ውስጥ [ክʸ፣ብʸ ፣ጥʸ ፣ትʸ ፣ስʸ] ሆነው መከሰታቸው ነው፡፡ /ክ/ እና /ብ/ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ የትናጋና የከናፍር ድምፆች ናቸው፡፡ /ጥ፣ት/ እና /ስ/ ደግሞ የድድ ድምፆች ናቸው፡፡ [ክʸ፣ብʸ ፣ጥʸ ፣ትʸ እና ስʸ] እንደ ቅደም-ተከተላቸው የእነዚሁ ድምፆች ከፊል ላንቃዊ አቻዎች ናቸው፡፡ ባጭሩ ላንቃዊ ያልነበሩት ድምፆች ወደ ከፊል ላንቃዊነት ተለውጠዋል ማለት ነው፡፡

ለዚህ ለውጥ ምክንያት የሆነው ነገር ምንድን ነው? ለምሳሌ ኪስንና [ክʸኢስ] እና ክይሲን [ክኸይስʸኢ] እያነፃፀርን እንመልከት፡፡ [ክʸኢስ] ውስጥ ያለችው [ክʸ] ከፊል ላንቃዊ ሆናለች፡፡ በመሆንዋም [ʸ] በሚል ምልክት ተጠቁማለች፡፡ [ክኸይስʸኢ] በሚለው ውስጥ ግን [ክ] ላይ የተጨመረ ምልክት የለም፡፡ ምልክት ያለው [ስʸ] ላይ ነው፡፡ [ክኸይስʸኢ] ውስጥ ያለችው [ክ] ላንቃዊ አይደለችም ማለት ነው፡፡ [ክʸኢስ] ውስጥ ያለችው [ክʸ] ላንቃዊ ስትሆን፣ [ክኸይስʸኢ] ውስጥ ያለችው [ክ] ለምን ላንቃዊ አልሆነችም? ለዚህ የምንሰጠው መልስ ከላይ ለጠየቅነውም ጥያቄ ምላሽ ይሆናል፡፡ መልሱ ከሁለቱ ድምፆች የአገባብ ልዩነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ [ክኸይስʸኢ] ውስጥ ያለችው [ክ] የገባችው [ኸ] ከሚለው የመሀል እናባቢ ቀድማ ነው፡፡ [ክʸኢስ] ውስጥ ያለችው [ክʸ] ግን የገባችው ከ[ኢ] በፊት ነው፡፡ ይህችም አናባቢ ላየኛና ፊተኛ ነች፡፡ ይህን ቀደም ሲል ከተሰጠው የአናባቢ ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡ [ክ] ወደ [ክʸ]

ድምፆች ወደ (ድ)ላንቃ ድምፅነት ተለውጠዋል፡፡ በድዳዊነትና በ(ድ)ላንቃዊነት መካከል ያለው ልዩነት ላየኛነት ነው፡፡ ይኸውም ድዳዊ የሆነ ድምፅ [- ላየኛ] ሲሆን፣ (ድ)ላንቃዊ የሆነ ድምፅ [+ ላየኛ] መሆኑ ነው፡፡ (ድ)ላንቃ የአፋችን ጣሪያ ስለሆነ፣ በዚያ ላይ የሚፈጠር ማንኛውም ድምፅ ]+ ላየኛ] ነው[15]፡፡ በዚህ መሰረት ከላይ በአዝባር ውስጥ የሚታዩት ድዳዊ ድምፆች በማዕዘኑ ውስጥ እንደሚታየው ወደ (ድ)ላንቃዊነት፣ ማለትም ወደ ላየኛነት፣ ተለውጠዋል፡፡ የለውጡ ምክንያት [+ ላይ] የሆነችው አናባቢ፣ ማለትም /-ኢ/፣ ነች፡፡ ይህች ድምፅ የላየኛነት ባህሪዋን ለድዳዊያኑ በማጋባት እነሱም [+ ላየኛ] እንዲሆኑ አድርጋለች፡፡ /ኢ/ [+ ላየኛ] የሆነችበት ምክንያት አፈጣጠርዋ የምላስን የፊት ክፍል ወደ ላይ፣ ማለትም ወደ (ድ)ላንቃ የሚያስነሳና ወደላይኛው የፊት ጥርስ የሚሰብ ስለሆነ ነው፡፡

በመለሰተኛው ላንቃዊነት [ት$^{ይ}$፣ ድ$^{ይ}$፣ ጥ$^{ይ}$፣ ሰ$^{ይ}$፣ ል$^{ይ}$፣ ን$^{ይ}$፣ ዝ$^{ይ}$] የነበሩት ድምፆች፣ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ በከፍተኛው ላንቃዊነት ወደ [ች፣ ጅ፣ ጭ፣ ሽ፣ ይ፣ ኝ፣ ወዘተ፣] ሊለወጡ ችለዋል፡፡ የመለለተኛዎቹ መካነ ፍጥረት አሁንም ድድ ሲሆን፣ የከፍተኛዎቹ መካነ ፍጥረት ወደ (ድ)ላንቃ ተለውጦአል፡፡ የባህሪ ብቻ ሳይሆን፣ የመካነ ፍጥረት ለውጥም አድርገዋል፡፡

የዚህ አይነት ለውጥ የሚታየው በአድራጊ ሰሞች ላይ ብቻ አይደለም፡፡ በተውላጠ ሰሞች፣ በቅፅሎችና በግሶች ላይም ይከሰታል፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን እያነፃፀርን እንመልከት፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| (ሀ) | አንተ | አንቺ | 2 |
| | ክለሰ | ክሰሺ | |
| (ለ) | ረዘመ | ረዥም | |
| | ቀጠነ | ቀጭን | |

በመጀመሪያው ረድፍ ከተዘረዘሩት መካከል የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ቃላት የመጨረሻ ተናባቢ ድምፆች /ት/ እና / ስ/ ናቸው፡፡ የሚቀጥሉት ሁለት ቃላት የመሀለኛ ድምፅ ደግሞ / ዝ/ እና /ጥ/ ናቸው፡፡ አራቱም ድምፆች ድዳዊ ናቸው፡፡ በሁለተኛው ረድፍ ውስጥ ባሉት ቃላት ውስጥ እነዚሁ ድምፆች ወደ (ድ)ላንቃዊነት ተለውጠው [ች፣ ሽ፣ ዥ፣ እና ጭ] ሆነዋል፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ድምፆቹ ከታቸኛነት ወደ ላየኛነት ተለውጠዋል፡፡ የለውጡ መንሰዔ አሁንም /ኢ/ ነች፡፡ የእያንዳንዳቸውን ታህታይ ቅርፅ እንመልከት፡፡

---

[15] (ድ)ላንቃ በሚለው ቃል መነሻ ላይ የሚታየው (ድ) በቅንፍ ውስጥ እንዲታይ የተደረገው ድምፆቹ ወደ ላንቃና ወይም ወደ ድላንቃ የሚለወጡ መሆናቸውን ለማሳየት ነው፡፡

የተሰለፈውን ድዳዊ /ን/ ወደ ትናጋዊነት እንዲለወጥ ምክንያት ሆነዋል፡፡ የለውጡን አካሄድ እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

$$\begin{bmatrix} -\text{ ላይ} \\ -\text{ ሁዋ} \\ +\text{ ሰ} \end{bmatrix} \rightarrow \begin{bmatrix} +\text{ ላይ} \\ +\text{ ሁዋ} \\ +\text{ ሰ} \end{bmatrix} \Big/ __ \begin{bmatrix} +\text{ ላይ} \\ +\text{ ሁዋ} \\ -\text{ ሰ} \end{bmatrix} \qquad 2$$

ቅምሩ አንድ የላይና የሁዋላ ያልሆነ የሰርን ድምፅ፣ ከአንድ የላይና የሁዋላ ከሆነ ድምፅ በፊት ሲገባ፣ የሁዋላና የሰርን ድምፅ ይሆናል የሚል ነው፡፡ ባጭሩ እንደ /ን/ ያለ የድድ ድምፅ እንደ /ግ/ ካለ የትናጋ ድምፅ ቀድሞ ሲግባ፣ እሱም እንደ ጎረቤቱ የትናጋ የሰርን ድምፅ ይሆናል፡፡

## ማንቁርታዊነት

ቀደም ሲል ስለ ድምፆች አፈጣጠር ስንወያይ፣ ማንቁርታዊ ድምፆች አየር በአፍ ውስጥና በማንቁርት ውስጥ በአንድ ጊዜ ታግዶ፣ በአንድ ጊዜ ሲለቀቅ፣ እንደሚፈጠሩ ገልፀን ነበር፡፡ በዚህ አይነት የሚፈጠሩት ድምፆች /ጭ፣ ጥ፣ ፅ፣ ጭ እና ቅ/ ናቸው፡፡ በቅንጅት ወቅት፣ ከነዚህ ድምፆች በፊት የሚገኝ ሌላ ድምፅ ከነሱ በሚመጣ ተጋቦት ምክንያት ማንቁርታዊ ሊሆን ይችላል፡፡ የዚህ አይነት የባህሪ ተጋቦት ሂደት ማንቁርታዊነት ይባላል፡፡ የሚከተሉት ሂደቱ የሚከሰትባቸው ቃላት ናቸው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| /አሰ-ፅ-ፍኧው/ | [አፅ-ፅእፍኧው] | አፅፊው | 1 |
| /አት-ጥኧይይ-ቅ/[16] | [አጥ-ጥኧይይእቅ] | አጠይቅ | |
| /አት-ጭኧቅጭ-ቅ/ | [አጭ-ጭኧቅጭእቅ] | አጩቅጭቅ | |
| /አት-ቅኧቅቅ-ል/ | [አቅ-ቅኧቅቅእል] | አቀቅል | |

/አሰ-/ በሚለው ምዕላድ መጨረሻ ላይ የሚገኘው /ሰ/ እና /ት/ ኢማንቁርታዊና ኢነዛሪ የድድ ድምፆች ናቸው፡፡ ከነሱ ቀጥለው የሚገኙት የየአምዱ መነሻ ድምፆች ማንቁርታዊና ኢነዛሪ ናቸው፡፡ በዚህ ጉርብትና ምክንያት፣ ማንቁርታዊ ያልነበሩት /ት/ እና /ሰ/ ማንቁርታዊ ለሆኑ ችለዋል፡፡ ሂደቱ /ሰ/ን ወደ [ፅ]፣ /ት/ን ወደ [ጥ]፣ እንዲሁም [ጭ] ን ወደ [ቅ] ለውጦታል፡፡ የ/ሰ/ ለውጥ የመካነ ፍጥረት ሳይሆን፣ የባህርየ ፍጥረት ነው፡፡ በመካነ ፍጥረትዋ / ሰ/ አሁንም ድዳዊ ነች፡፡ የ/ት/ ለውጥ ግን የሁለቱም ነው፡፡ ምክንያቱም /ት/ በመሰረታዊ ፍጥረትዋ

---

[16] የእነዚህ ቃላት ታህታይ ቅርፅ /አል-ት-ጥኧይይ-ቅ/፣ /አል-ት-ጭኧቅጭ-ቅ/፣ /አል-ት-ቅኧቅቅ-ል/ ነው፡፡ ከ/-ት-/ በፊት ገብታ የምትገኘው /-ል/ በታህታይ ቅርፅ ላይ ትገደፋለች፡፡ የ/አሰ-ፅ-ፍኧው/ ባህሪ ከነዚህ የተለየ ነው፡፡ ሂደቱን ወደፊት እናየዋለን፡፡

አትታይም፡፡ ተገድፋለች ማለት ነው፡፡ በቀጥታ ከግሱ አምድ ላይ በምትገኝበት ጊዜ ግን በግሀድ ትታያለች፣ አትገደፍም ማለት ነው፡፡ ስለዚህም አልቀረበም ([አልቅኧርርኧብኧም]) በሚለው ውስጥ በግሀድ ስትታይ፣ አይቀርብም ([አይቅኧርብአም]) በሚለው ውሰጥ ግን አትታይም፡፡

አንድ መደብ አመልካች ቅጣይ ከግስ አምድ መነሻ ላይ የሚገኘው በካልዓይ አንቀፅ፣ በአምድ መድረሻ ላይ የሚገኘው ደግሞ በቀዳማይ አንቀፅ ግስ በሰሆን፣ የግድፈቱን አውድ ከዚሁ የአንቀፅ ልዩነት ጋር ማያያዝ ይቻላል፡፡ ከዚህም አአኩዋያ /ል/ የምትገደፈው በካልዓይ አንቀፅ ግስ ውስጥ ነው፣ ብሉ ማጠቃሰል ይችላል፡፡ ይህም ቀደም ሲል የ/ው፣ይ፣ህ፣ዕ/ን የግድፈት አኣውድ ከተሰየ የቃል ክፍል፣ ማለትም ከግስነት፣ ጋር እንዳያያዝነው ሁሉ፣ አአሁንም የ/ል/ን ግድፈት ከተወበን የግስ አኣምድ አኣይነት፣ ማሰትም ከካልዓይነት ጋር ማያያዛችን፣ የግድፈቱ ሂደት በሰነ-ድምፃዊ አኣውድ ላይ ሳይሆን፣ በሰነ-ምዕ ላዳዊ ቅርፅ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ ሰለ ቀዳማይና ካልዓይ አአንቀፅ በሚቀጥለው ምዕራፍ በሰፊው እንወያያለን፡፡

## ኢድምፀት

ቀደም ሲል ድምፆች በተፈጥሮአቸው ነዛሪና ኢነዛሪ ተብሰው በሁለት እንደሚከፈሉ ገልፀናል፡፡ በዚህ ልዩነት ምክንያት ነዛሪ ድምፆች [+ ድምፅ] ኢነዛሪዎቹ ደግሞ [ - ድምፅ] ተብለው ይመደባሉ፡፡ አንድ ነዛሪ የሆነ ድምፅ ነዛሪ ካልሆነ ሌላ ድምፅ ጋር ሲገባ፣ የባህሪ መወራረሰ ይከሰታል፡፡ ይኸውም ከፍ ሲል እንዳየነው፣ ኢነዛሪ የነበረው ነዛሪ ሊሆን፣ ወይም በተቃራኒው ነዛሪ የነበረው ኢነዛሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ኢነዛሪ የነበረን ድምፅ ነዛሪ የሚያደርግ ሂደት ድምፀት እንደሚባል ሁሉ፣ ነዛሪ የነበረን ድምፅ ኢነዛሪ የሚያደርገው ሂደት ኢድምፀት ይባላል፡፡ የሚከተሉት የዚህ የሁለተኛው ሂደት ምሳሌዎች ናቸው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| /ፍኧልልኧግ-ክ/ | [ፍኧልልኧክክ] | ፈለክ | 1 |
| /ድኧንኧዝዝኧዝ-ክ/ | [ድኧንኧዝዝኧሰክ] | ደነዘዝክ | |
| /አል-ት-ዕውጥአ/ | [አትትውጥአ] | አትውጣ | |

በአዝባሩ ውስጥ በሚታዩት የመጀመሪያ ምሳሌዎች፣ የየአምዱ የመጨረሻ ድምፅ፣ ማለትም /ግ/ እና /ዝ/፣ ነዛሪ፣ ሰለዚህም [+ ድምፅ] ናቸው፡፡ ከነዚህ ቀጥላ የምትታየው /-ክ/ ግን ኢነዛሪ እናም [ - ድምፅ] ነች፡፡ በከትትሉሹ ምክንያት የ/-ክ/ ኢነዛሪያዊ ባህሪ ወደ ቀዳሚው ድምፅ ይጋባል፡፡ በዚህም ምክንያት /ግ/ እና /ዝ/ እንደ ቅደም-ተከተላቸው ወደ [ክ] እና [ሰ] ሊለወጡ ችለዋል፡፡ በመጨረሻው ምሳሌም የአሉታዊው ምዕላድ የመጨረሻ ድምፅ

የሆነችው /ል/ ከአሰዋ ቀጥላ በምትገኘውና ኢነዛሪ በሆነችው በ/ት/ ምክንያት፣ እሰዋም ወደ ኢነዛሪነት ተለውጣ፣ በማዕዘኑ ውስጥ እንደሚታየው [ት] ሆናለች፡፡

ከዚህ ላይ ቀደም ሲል የአሉታዊው ምዕላድ የመጨረሻ ድምፅ የሆነችው /ል/ መደብ አመልካች ከሆነችው ምዕላድ ከ/ት-/ቀድማ ስትገባ ትገደፋለች ብለን ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ይህችው ድምፅ ማለትም /ል/ ወደ ኢነዛሪነት ትለወጣለች እያልን ነው፡፡ እነዚህ የሚጣረሱ ሀሳቦች ይመስላሉ፡፡ በአንድ በኩል ግድፈት፣ በሌላ በኩል ኢድምፀት ይካሄድበታል ማለታችን ነው፡፡ እነዚህ ሁለት የተለያዩ ሂደቶች በአንድ ድምፅ ላይ ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ የግድፈቱንና የኢድምፀቱን እውድ መለየት ግን ያስፈልጋል፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ ግድፈቱ የሚከሰተው በካልዓይ አንቀፅ ላይ ነው፡፡ ኢድምፀት ግን የሚከሰተው በትዕዛዝ አንቀፅ ላይ ነው፡፡

ተመሳሳይ የኢድምፀት ሂደት በአናባቢዎች ላይም ይከሰታል፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| /ጥኧግግኧብክ-ኡ/ | [ጥኧግግኧብክኡ$^{ሣ}$] | ጠገብኩ | 2 |
| /ውኧጥጥኣህ-ኡ/ | [ውኧጥጥኣህኡ$^{ሣ}$] | ወጣሁ | |

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የመጨረሻው አናባቢ ድምፅ /ኡ/ ነው፡፡ እንደማንኛውም አናባቢ ድምፅ በመሰረተ ባህሪው ነዛሪ ብሎም [+ ድምፅ] ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ በማዕዘኑ ውስጥ እንደሚታየው፣ ወደ ኢነዛሪነት ተለውጦ [ኡ$^{ሣ}$] ሆኗአል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ፣ ድምፁ ኢነዛሪ ከሆኑት ከ/ክ/ እና ከ/ህ/ ቀጥሎ መገኘቱና የእነሱ የኢነዛሪነት ባህሪ ወደሱ መጋባቱ ነው፡፡ የተጋቦቱ አቅጣጫ ግን ከፍ ሲል ከሚታየው የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም የላይኛው ሂደት መላሽ ያልነው አይነት ሲሆን፣ ይኸኛው ግን ቀደም ሲል የጠቀስነው የገስጋሽ ምስስሉሽ ምሳሌ ነው፡፡ ባህሪው የሚጋባው ወደፊት ማለትም ወደ ቀኝ ሄዶ ነውና፡፡

የሁሉንም ኢድምፀታዊ ሂደቶች ጠቅለል አድርጎ በአንድ ቅምር ማሳየት አስቸጋሪ ነው፡፡ አንደኛ ባህሪው ሚሄድበት የአቅጣጫ ልዩነት አለ፡፡ ሁለተኛም በቅምሩ ውስጥ ሲካተቱ የማይችሉ ምሳሌዎች ያጋጥሙናል፡፡ እነዚህም እንደ *ወደድክ* ([ውኧድድኧድክ]) እና *ወሰድክ* ([ውኧሰሰኧድክ]) ያሉት ቃላት ናቸው፡፡ ከፍ ሲል ባየነው አካሄድ መሰረት፣ በነዚህ ቃላት ውስጥ ከ/ክ/ በፊት የሚገኘው /ድ/ ወደ ኢነዛሪነት ተለውጦ [ት] መሆን ነበረበት፣ ግን ነዛሪነቱን እንደጠበቀ ይገኛል፡፡ በቅምሩ መሰረት ድምፁ ወደ ኢነዛሪነት ቢለወጥ ኖሮ፣ የቃላቱ ቅርፅ [ውኧድድኧትክ] እና [ውኧሰሰኧትክ] ይሆንና ተቀባይነትን ያጣ ነበር፡፡ በጥቅሉ ግን አንድ ነዛሪ የነበረ ድምፅ ኢነዛሪ ከሆነ ሌላ ድምፅ ቀድሞ ወይም ተከትሎ ሲገኝ፣ ወደ ኢነዛሪነት ይለወጣል የሚሉ ቅምሮችን እንደሚከተለው አድርጎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ተፈፃሚነቱን ሂደቱ በሚታይባቸው ቃላት ላይ ብቻ መወሰን ይቻላል፡፡

(ሀ) $$\begin{bmatrix} +\text{ተ} \\ +\text{ድምፅ} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} +\text{ተ} \\ -\text{ድምፅ} \end{bmatrix} / ___ \begin{bmatrix} +\text{ተ} \\ -\text{ድምፅ} \end{bmatrix}$$ 3

(ለ) $$\begin{bmatrix} +\text{ድምፅ} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} -\text{ድምፅ} \end{bmatrix} / \begin{bmatrix} +\text{ተ} \\ -\text{ድምፅ} \end{bmatrix} ___$$

የመጀመሪያው ቅምር ነዛሪ የሆነ ተናባቢ ድምፅ ኢነዛሪ ከሆነ ተናባቢ ድምፅ በፊት ሲገኝ ወደ ኢነዛሪነት ሲለወጥ እንደሚችል፣ ሁለተኛው ግን ነዛሪ የሆነ ድምፅ ኢነዛሪ ከሆነ ተናባቢ በሁዋላ ሲገኝ ወደ ኢነዛሪነት ሲለወጥ እንደሚችል ያሳያል፡፡ ይህ ህግ እናባቢንም ያጠቃልላል፡፡

## ግድፈት

በተጎራባች ድምፆች መካከል የባህሪ መወራረስ ብቻ ሳይሆን፣ አንዱ በሌላው ምክንያት ከቦታው የመጥፋት ሂደትም ሊደርስበት ይችላል፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን እንደ አዘነ፣ አየለ፣ አነፀ፣ ወዘተ፣ ያሉት ግሶችና እንደ ሀገር፣ ሀሞት፣ ወዘተ ያሉ ስሞች ናቸው፡፡ የግሶቹ ታህታይ ቅርፅ፣ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣/ህኧዝዝኧንኧ/፣ /ህኧይይኧልኧ/፣ /ህኧንንኧፅኧ/ ነው፡፡ ይህ ለመሆኑ ማስረጃው፣ በየግሶቹ ስማዊ እቻ ላይ /ህ/ የሚለው የየቃሉ የመነሻ ድምፅ በግልፅ መታየቱ ነው፡፡ ለምሳሌ የ/ህኧዝዝኧንኧ/ ስማዊ እቻ ህዘን ([ህአዝኧን]) ሲሆን፣ የ/ህኧይይኧልኧ/ ደግሞ ሀይል ([ህአይል]) ነው፡፡ ሌላው ማስረጃ የግሶቹ የመጀመሪያ ላዕላይ ድምፅ እናባቢ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ከቋንቋው አጠቃላይ የግስ ባህሪ የሚያፈነግጥ ሁኔታ ነው፡፡ ከተወሰኑት በስተቀር፣ የአማርኛ ግሶች በተናባቢ እንጅ በእናባቢ አይጀምሩም፡፡ ለምሳሌ፣ እንደ ገደለ፣ ሰበረ፣ ዘመረ፣ ወዘተ ያሉ ግሶች በተናባቢ የሚጀምሩና፣ ከዚያ ተናባቢ ቀጥሎም /ኧ/ የሚለውን የመሀል አናባቢ የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ የገደለ ታህታይ ቅርፅ /ግኧድድኧልኧ/ ነው፡፡ በግልፅ እንደሚታየውም፣ የመጀመሪያው ድምፅ ተናባቢ ሲሆን ከእሱ ቀጥሎ የሚታየው አናባቢ ደግሞ ሌላ ሳይሆን፣ /ኧ/ ነው፡፡ ይህም መሀለኛ አናባቢ ነው፡፡ የቃሉ ላዕላይ ቅርፅም የሚጀምረው እንደዚሁ በተመሳሳይ ተናባቢ ድምፅ ነው፡፡

/ህኧዝዝኧንኧ/ በሚለው ቅርፅ መጀመሪያ ላይ የሚገኘው ተናባቢ፣ ማለትም /ህ/፣ ከ/ኧ/ በፊት ሲገባ፣ ባህሪውን ለአናባቢው ድምፅ ሰጥቶ፣ እሱ ከቦታው ይጠፋል፡፡ የ/ህ/ ባህሪ ታቸኛነት ነው፡፡ የታች ድምፅ ነው፣ ማለት ነው፡፡ የታች የሚባልበት ምክንያት፣ ድምፁ ማንቁርት ውስጥ ሲፈጠር ምላስ ወደታች ዝቅ ብሎ ስለሚገኝ ነው፡፡ ይህ ታቸኛ ድምፅ ከፍ ሲል ከተገለፀው መሀለኛ ከሆነው ከ/ኧ/ በፊት ሲገባ፣ የታቸኛነት ባህሪውን ለ/ኧ/ ሰጥቶ፣ እሱ ከዚያ ቦታ ይጠፋል፡፡

የታቸኛነት ባህሪን የተላበሰው /ኸ/ም ከመሀለኛነት ወደ ታቸኛነት ይለወጥና [እ] ይሆናል፡፡ ዝርዝሩን በመተው አአጠቃላይ ለውጡን ብቻ እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

$$(\text{ሀ})\quad \begin{bmatrix} +\text{አ} \\ -\text{ታ} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} +\text{አ} \\ +\text{ታ} \end{bmatrix} \Big/ \begin{bmatrix} -\text{አ} \\ +\text{ታ} \\ +\text{ሁዋ} \end{bmatrix} __ \qquad 1$$

$$(\text{ለ})\quad \begin{bmatrix} -\text{አ} \\ +\text{ታ} \end{bmatrix} \longrightarrow \emptyset \Big/ __ \begin{bmatrix} +\text{አ} \\ +\text{ታ} \end{bmatrix}$$

አ = እናባቢ ታ = ታች

ህጎቹ ተከታታይና ተደጋጋፊ ናቸው፡፡ መጀመሪያ /ኸ/ በ/ሀ/ ምክንያት ወደ [እ] ይለወጣል፡፡ ከዚያ በሁዋላ፣ /ሀ/ በ[እ] ምክንያት ከቦታው ይጠፋል፡፡ ሂደቱ በከፊል የምስስሎሽ በከፊል ደግሞ የግድፈት ነው፡፡ ምስስሎሹ ለግድፈቱ መንስዔ ሆኖአል፡፡

በ/ሀ/ ምክንያት በ/ኸ/ ላይ የደረሰው ለውጥ ቀደም ሲል የጠቀስነው የገስጋሽ ምስስሎሽ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ /ሀ/ የታቸኛነት ባህሪዋን በቀኟዋ በኩል ለሚገኘው ለ/ኸ/ አጋብታ ጠፍታለች፡፡ የመሀለኛ እናባቢ የነበረችው /ኸ/ም በተጋቦቱ ምክንያት ታቸኛ ልትሆን ችላለች፡፡ ሌላም የዚህ አይነት ምሳሌ ስለ <u>ትናጋዊነት</u> ስንወያይ እንመለከታለን፡፡

/ሀ/ የምትገደፈው ከላይ እንደሚታየው በቃል መነሻ ላይ ብቻ አይደለም፡፡ በቃል መካከልና በቃል መድረሻም ጭምር ነው፡፡ በሁለቱም ቦታዎች የታቸኛነት ባህሪዋን ተከትሎአት ለሚገባው ድምፅ ሰጥታ እስዋ ከቦታዋ ትጠፋለች፡፡ የሚከተሉት ቃላት ለዚህ ምሳሌ ናቸው፡፡

ማለ 2
ዓፈ

የእነዚህ ቃላት ታህታይ ቅርፅ እንደ ቀደም-ተከተላቸው፣

/ምኸሀኸልኸ/[18] 3
/ፅኸሀኸፍኸ/

---

[18] ቀደም ሲል እንደተገለፀው /ሀ/ ጠባቂ ድምፅ አይደለችም፡፡ ብትሆን ኖሮ፣ የግሱ ቅርፅ /ምኸሀሀኸልኸ/ ይሆን ነበር፤ ይህ ደግሞ ትክክለኛ አባባል አይደለም፡፡

ነው፡፡ በየታህታይ ቅርፃቸው ውስጥ/ህ/ ስመኖሩ ማስረጃው፣ በነዚህ ግሶች ስማዊ አቻ ውስጥ /ህ/ በግህድ መታየቱ ነው፡፡ ይኸውም ስምሳሌ፤ መሀላ እና ፀሀፊ ስንል ነው፡፡ ሁለተኛም በየግሶቹ ውስጥ የሚገኘው የመጀመሪያው እናባቢም ቅርፁ ከ/ኧ/ ወደ /አ/ መለወጡ ተጨማሪ ማስረጃ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው፣ /ህ/ የታቸኛነት ባህሪውን ለ/ኧ/ ሲሰጥ፣ መሀለኛ የነበረው /ኧ/ ወደ ታቸኛነት ይለወጥና [እ] ይሆናል፡፡ በነዚህ ምሳሌዎችም በግህድ የሚታየው ይኸው ሁኔታ ነው፡፡

ምሳሌዎቹ በቃል መካከል የሚገኝ /ህ/ ባህሪውን ለጎረቤቱ እየሰጠ ሲጠፋ፣ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በቃል መድረሻም ቢሆን እንደዚሁ ባህሪውን እየሰጠ ሲጠፋ የሚያሳዩ ምሳሌዎች አሉ፡፡ እነሱም እንደ፣

በራ 4
ፊራ

ያሉ ቃላት ናቸው፡፡ የእነዚህ ታህታይ ቅርፅ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣

/ብኧርርኧህኧ/ 5
/ፍኧርርኧህኧ/

ነው፡፡ ይህ ውነት ስመሆኑ አሁንም ማስረጃው የየግሶቹ አቻ የሆኑት ስሞች /ህ/ን በግልፅ ማሳየታቸው ነው፡፡ ይኸውም፣

ብርሃን 6
ፍርሃት

ስንል ነው፡፡ በግሶቹ ውስጥ በጠፋበት ቦታ ላይ፣ በየአቻ ስሞቹ ውስጥ ሊከሰት ችሉአል፡፡ ሁለተኛም እንደ በራ ያሉ የመጨረሻ ተናባቢያቸውን የሚጥሉ ግሶች በአርዕስታዊ፣ በቦዝ አንቀፃዊና በአጠንካሪ አቻ ቅርፆቻቸው ላይ፣ [ት]ን በምትክነት ያሳያሉ፡፡ የሚያሳዩትም በግሱ ስር ድምፅዋ በተገደፈችበት ቦታ ላይ ነው፡፡ ስምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| ስር | ግስ | አርዕስት | ቦዝ | አጠናካሪ | |
|---|---|---|---|---|---|
| /ብ-ር-ህ/ | /ብኧርር-/ | /ምኧብርአት/ | /ብኧርት-ኦ/ | [ብአርርአትት] | 7 |
| /ፍ-ር-ህ/ | /ፍኧርር-/ | /ምኧፍርአት/ | /ፍኧርት-ኦ/ | [ፍእርርእትት] | |
| /ስ-ር-ህ / | /ስኧርር-/ | /ምኧስርአት/ | /ስኧርት-ኦ/ | [ስእርርእትት] | |
| /ብ-ል-ዕ/ | /ብኧልል-/ | /ምኧብልአት/ | /ብኧልት-ኦ/ | [ብእልልእትት] | |

በእርዕስት፣ በቦዝ እና በአጠንካሪ አምዶች ውስጥ የሚገኘው የመጨረሻ ድምፅ [ቷ[ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ይህ ድምፅ በየእቻ ግሶቹ ታህታይ ቅርፅ ውስጥ መጨረሻ ላይ የሚገኘውና በላዕላይ ቅርፁ የተገደፈው የ/ህ/ ወይም የ/ዕ/ ምትክ ነው፡፡ ሁኔታው አንድ በታህታይ ቅርፅ ውስጥ የሚገኝ ድምፅ ያለምንም ምትክ ወይም ምልክት ከቦታው ሊጠፋ እንደማይችል ያመለክታል፡፡ ከዚህ ሁኔታ፣ [ት[ የተገዳፊ ድምፅ ቤት ጠባቂ እንደሆነች ለመረዳት ይቻላል፡፡

[ት] ምትክ ወይም ቤት ጠባቂ እየሆነች በየአምዱ መጨረሻ ላይ የምትገባው በግሱ ስር መጨረሻ ላይ ለሚገደፍ ተናባቢ ድምፅ ብቻ አይደለም፡፡ በጣም ውሱን በሆኑ ግሶች ውስጥ፣ የመጀመሪያ ተናባቢ በነበረና በተገደፈ ድምፅ ምትክ ልትገኝ ትችላለች፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን እየ እና እለ [እልልኧ] የሚሉት ግሶች ናቸው፡፡ የነዚህ ግሶች ታህታይ ቅርፅ የሚጀምረው እንደ ቅደም-ተከተላቸው በ/ር/ እና በ/ህ/ ነው፡፡ ይህ ውነት ለመሆኑ ሁለት ማስረጃዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው የየቃላቱ ታሪካዊ አመጣጥ ሲሆን፣ ሁለተኛው የእቻ ስሞቻቸው ላዕላይ ቅርፅ ነው፡፡ ታሪካዊ አመጣጣቸው፣ አሁንም እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ /ር-ዕ-ይ/ እና /ህ-ል-ው/ ከሚሉ ስሮች ነው፡፡ እነዚህ ስሮች በግዕዝ ርዕየ እና ህለወ የሚል ግላዊ ቅርፅ አላቸው፡፡ በአማርኛ ደግሞ በየስሩ ከሚገኙት ድምፆች የተወሰኑትን ጥለው፣ ከላይ በሚታዩበት ቅርፃቸው እየ እና እለ [እልልኧ] ሆነው ይገኛሉ፡፡ የነዚህ ግሶች ለማዊ እቻዎች ግን የተገደፉትን ድምፆች በላዕላይ ቅርፃቸው ውስጥ ያሳያሉ፡፡ እነዚህም ራዕይ እና ህልውና ናቸው፡፡ የየግሶቹ አርዕስታዊ ቅርፅም በመድረሻቸው ላይ በግሶቹ መነሻ ላይ በተገደፉት ተናባቢዎች ምትክ [ት]ን ያሳያሉ፡፡ ይኸውም እየ ብለን፣ ማየት ስንል ነው፡፡ ርግጥ፣ በዚሁ አካሄድ እለ [አልልኧ] ብለን፣ ማለት [ምአልልኧት] ማለት ነበረብን፡፡ የምንለው ግን መኖር ነው፡፡ ይህ ደግሞ የኖረ አርዕስታዊ እቻ እንጅ የእለ አይደለም፡፡ እለ የራሱ የሆነ አርዕሰታዊ እቻ የለውም[19]፡፡

የመሀል ተናባቢ ድምፃቸውን የሚገድፉ ግሶች በአርዕሰታዊ እቻቸው መድረሻ ላይ [ት]ን አያሳዩም፡፡ ስለዚህም የማለ አርዕስታዊ ቅርፅ መማል እንጅ መማለት አይደለም፡፡ ባህሪውን ለቀዳሚ ጎረቤቱ ሰጥቶ የሚጠፋው ድምፅም /ህ/ ብቻ አይደለም፡፡ እንደሉ የማንቁርት ድምፅ የሆነው /ዕ/ም እንደዚሁ የታቸኛነት ባህሪውን ለጎረቤቱ እየሰጠ ይጠፋል፡፡ ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

ሳለ 8
በላ

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የተገደፈው ድምፅ /ዕ/ ነው፡፡ ይህ ለመሆኑ ማስረጃው አሁንም ታሪካዊ ነው፡፡ ሁለቱም ቃላት እንደ ቅደም-ተከተላቸው ሰዓለ እና በልዓ የሚል ግዕዛዊ እቻ አላቸው፡፡ በአማርኛም ቢሆን በተለይ ሳለ የሚለው ግስ

[19] የሁለቱን ግሶች ታህታይ አቀነጃጀትና ላዕላይ ለውጥ በተመለከተ ዝርዝሩን ከባየ (1997፤ 1999) ይመልከቱ፡፡

በስማዊ አቻው ውስጥ /ዕ/ን በግሀድ ያሳያል፡፡ ይኸውም <u>ለዕል</u> በምንልበት ጊዜ ነው፡፡

/ዕ/ የተገደፈው በመጀመሪያው ግስ መሀልና በሁለተኛው ግስ መድረሻ ላይ ነው፡፡ በሁለተኛው ግስ ላይ ድምፁ የተገደፈው መድረሻ ላይ በመሆኑም የዚሁ ግስ አርዕስታዊ ቅርፅ፣ በተገደፈው ድምፅ ቦታ ላይ [ት]ን በምትክነት ያሳያል፡፡ ይኸውም <u>በላ</u> ብለን <u>መብላት</u> ስንል ነው፡፡ ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይኸውም /ዕ/ በመሀልና በመድረሻ እንደምትገደፍ ሁሉ፣ በመነሻስ ልትገደፍ ትችላለች ወይ? የሚል ነው፡፡ የዚሁ ተከታይ ሊሆን የሚችለው ሌላ ጥያቄ ደግሞ፣ /ዕ/ በግስ መነሻ ላይ የምትገደፍ ከሆነ፣ በአርዕስታዊ አቻው ላይ በ[ት] ትተካለች ወይ? የሚል ነው፡፡ በርግጥ /ዕ/ በአንዳንድ ግሶች መነሻ ላይ ትገደፋለች፡፡ ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

አወቀ 9
አበደ

የእነዚህ ግሶች መነሻ /አ/ የሚለው ታችኛ አናባቢ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ የአማርኛ ግሶች ታህታይ ቅርፅ በተናባቢ እንጅ በአናባቢ አይጀምርም፡፡ በዚሁ መሰረት የነዚህ ግሶች ታህታይ ቅርፅም እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣

/ዕኧውውኧቅኧ/ 10
/ዕኧብብኧድኧ/

መሆን ይኖርበታል፡፡ የሁለቱም መነሻ አግድ የማንቁርት ድምፅ የሆነው /ዕ/ ነው፡፡ ይህ ድምፅ እንደ /ህ/ የታችኛነት ባህሪውን ከእሱ ቀጥሎ ለገባው መሀለኛ አናባቢ፣ ማለትም ለ/ኧ/ ይሰጥና ከቦታው ይጠፋል፡፡ የእሱን ባህሪ የወለደው /ኧ/ ከመሀለኛነት ወደ ታችኛነት ተለውጦ [አ] ይሆናል፡፡ ይህ ቀደም ሲል ካየው ከ/ህ/ ሁኔታ ጋር አንድ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ /ዕ/ም ሆነ /ህ/ በመነሻ ላይ ሲገደፉ፣በሚገደፉበት አርዕስታዊ አቻ መድረሻ ላይ [ት]ን በምትክነት አያሳዩም፡፡ ለለዚህም የግሶቹ አርዕስታዊ አቻዎች <u>ማወቅ</u> እና <u>ማበድ</u> ናቸው፡፡ [ት]ን በመድረሻቸው ላይ ቢጨምሩ፣ <u>ማውቀት</u> እና <u>ማብደት</u> ይሆኑ ነበር፡፡ እነዚህ ደግሞ ተቀባይነት ያላቸው የአማርኛ ቃላት አይደሉም፡፡ ከዚህ የምንረዳው በአርዕስታዊ አቻቸው ላይ [ት]ን በምትክነት የሚያስገቡት እንደ <u>አየ</u> ያሉት የመነሻ ተናባቢ ድምፃቸውን ባህሪ ለሚቀጥለው አናባቢ ድምፅ ሳያጋቡ የሚገደፉት ብቻ መሆናቸውን ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው፣ የ<u>አየ</u> የመጀመሪያ ድምፅ /ር/ ነው፡፡ ይህ ድምፅ ከመነሻ ቦታው የጠፋው ያለምንም <u>ዱካ</u> ነው፡፡ ስለዚህም በግሉ መነሻ ላይ የተጎረደ ድምፅ እንዳለ ለማሳየት በአርዕ-ስቱ መድረሻ ላይ [ት]ን ያሳያል፡፡ ዝርዝሩን አሁንም ከባየ (1999) ላይ ይመልከቱ፡፡

የግድፈት ሂደት የሚታይባቸው ሌሎች ቃላትም አሉ፡፡ እነሱም እንደ ሸጠ እና መሸ ያሉት ግሶች ናቸው፡፡ በነዚህ ቃላት ላዕላይ ቅርፅ የሚገኙት እናባቢዎች [ኧ] እና [ኤ] ናቸው፡፡ በዚህም ቀደም ሲል ካየናቸው ገዳፊ ቃላት ይለያሉ፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል ባየናቸው ቃላት ላዕላይ ቅርፆች ውስጥ ያየናቸው እናባቢዎች [ኧ] እና [አ] ስለነበሩ ነው፡፡ ለምሳሌ፡ በላ በሚለው ቃል ውስጥ መጀመሪያ [ኧ]ን ቀጥሎ ደግሞ [አ]ን ስናገኝ፣ ማለ በሚለው ቃል ውስጥ ደግሞ መጀመሪያ [አ]ን፣ ቀጥለን [ኧ]ን እናገኛለን፡፡ የእናባቢዎቹ መለያየትና የተናባቢዎቹ ሁለት ብቻ መሆንም፣ በየቃሉ ውስጥ አንድ ተናባቢ ድምፅ እንደ ተገደፈ ሊጠቁም ይችላል፡፡ የተናባቢዎቹ ሁለት ብቻ መሆን ግን ብቻውን የግድፈት ምልክት ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ከስረ-መሰረታቸው ባለሁለት ተናባቢ የሆኑ እንደ ተወ ያሉ ቃላት በቋንቋዋው ውስጥ ስለሚገኙ ነው[20]፡፡

ከዚህ ላይ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ታዲያ እንደ ሸጠ እና መሸ ያሉት ቃላትስ ቢሆኑ አንድ ተናባቢ ለመግደፋቸው ማስረጃው ምንድን ነው? እነዚህስ ቢሆኑ ከስረ-መሰረታቸው እንደ ተወ ባለሁለት ተናባቢ ሊሆኑ አይችሉም ወይ? የሚል ነው፡፡ እንደ ሸጠ ያሉትን ባለሁለት ተናባቢ ናቸው እንዳንልማ፣ እንደ ተወ ካሉት ባለሁለት ተናባቢ የሚለዩበት አንድ ባህሪ አላቸው፡፡ ይኸውም በአርዕስታዊ ቅርፃቸው ላይ [ት] የምትለዋን ቤት ጠባቂ ድምፅ ማሳየታቸው ነው፡፡ ስለዚህም መሸ ብለን መምሸት እንደምንል ሁሉ፣ ተወ ብለን መተው እንጅ መተውት አንልም፡፡ ከዚህም በመነሳት እንደ መሸ ያሉት ግሶች በታህታይ ቅርፃቸው ባለሁለት ሳይሆኑ፣ ባለሶስት ተናባቢ ናቸው ለማለት እንችላለን፡፡ ከተናባቢዎቻቸውም መካከል የመጨረሻውን፣ ማለትም ሶስተኛውን፣ ተናባቢ ይገድፋሉ፡፡ ተገዳፊው እሱ ባይሆን ኖሮ፣ በአርዕስታዊ ቅርፃቸው ላይ [ት] አትታይም ነበር፡፡ ይህች ድምፅ ምትክነትዋ በቃል መጨረሻ፣ አንዳንድ ጊዜም በቃል መነሻ ላይ ለሚገደፍ ድምፅ ነው ብለናልና፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ሊነሳ የሚችለው ሌላ ጥያቄ የተገደፈው ድምፅ ምንድን ነው? የሚል ነው፡፡ ቀደም ሲል ያየነው /ህ/ ወይም /ዕ/ ሊሆን አአይችልም፡፡ ቢሆን ኖሮ፣ ድምፁ ታቸኛ ስለሆነ፣ ይህን የታቸኛነት ባህሪውን ቀድሞት ለሚገባው እናባቢ፣ ማለትም ለ/ኧ/ ሰጥቶ ሲጠፋ፣ እናባቢው ወደ [አ] ተለውጦ፣ የየቃላቱ ላዕላይ ቅርፅ ሻጠ እና መሻ መሆን ነበረበት፡፡ ይህ አለመሆኑ፣ ተገዳፊው ድምፅ የታቸኛነት ባህሪ ያለው እንደ /ህ/ ወይም /ዕ/ ያለ ተናባቢ

---

[20]ይህን ጉዳይ አለመልከቶ ባየ (1999) ሁሉም የአማርኛ ግሶች በታህታይ ቅርፃቸው ባለሶስት ተናባቢ ብቻ እንደሆኑ ይገልፃል፡፡ በዚህ አመለካከት መሰረት፣ እንደ ተወ ያሉትም ባለሶስት ተናባቢ ናቸው፡፡ የመጨረሻው ተናባቢ ለመገደፉ ምልክቱ፣ በተወ አጠንካሪና አለሳላሽ ቅርፅ ላይ [ት] በምትክነት ብቅ ማለትዋ ነው፡፡ ምንም ድምፅ ባልጎረዱ እንደ ሰበረ ባሉ ግሶች አጠንካሪና አለሳላሽ ቅርፅ ምንም ምትክ ድምፅ አይገኝም፡፡ ስለዚህም ሰበረ ብለን ሰብር አንጅ ሰብርት አንልም፡፡ ተወ ብለን ትውት እንደምንለው ማለት ነው፡፡ ሸጠ ብለን መሸጥት ወይም ሸጥት አንልም፣ ምክንያቱም /ት/ በምትክነት የምትገባው በቃል መጨረሻ ላይ ለተጎረደ ድምፅ ነው፡፡ ሸጠ የጎረደው መካከለኛ ተናባቢውን ነው፡፡

ድምፅ እንዳልሆነ ይጠቁመናል፡፡ የተገደፈው ደምፅ ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ መልሳችን /ይ/ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ውነት ከሆነ፡ የቃላቱ ታህታይ ቅርፅ፣

/ምኧሰለኧይኧ/ 11
/ለኧይይኧጥኧ/

መሆን አለበት፡፡

ታህታይ ቅርፃቸው ይህን ከመሰለ፣ ላዕላይ ቅርፃቸው መሸ እና ሸጠ ሊሆን የቻለው እንዴት ነው? ቀደም ሲል አንድ በታህታይ ቅርፅ ውስጥ የሚገኝ ድምፅ ከላዕላይ ቅርፅ የሚጠፋው ባህሪውን አጠገቡ ለሚገኝ ድምፅ አውርሶ ነው፣ ብለን ነበር፡፡ በዚያ መሰረት መሸ ውስጥ /ይ/ የተገደፈው ባህሪውን ለ/ኧ/ እና ለ/ሰ/ ከሰጠ በሁዋላ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ የ/ይ/ ባህሪ ላየኛነትና ፊተኛነት ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ድምፁ የሚፈጠረው ላንቃ ላይ ስለሆነና ላንቃ ደግሞ፣ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የአፋችን መሀል ጣሪያ መሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም [ይ] ስንል፣ የምላሳችን የፊት ክፍል ወደ ላይ፣ ማለትም ወደ ላንቃ ብቻ ሳይሆን፣ ወደፊት፣ ማለትም ወደ ላይኛው የውስጥ ድዳችን ክፍል ስለሚሳብ፣ ድምፁ የፊተኛነት ባህሪም አለው፡፡ ስለዚህም ላየኛነትንም ሆነ ፊተኛነትን አጣምሮ የያዘ ድምፅ ነው፡፡ ባንፃሩ ደግሞ /ኧ/ እና /ሰ/ የላንቃ ድምፆች አይደሉም፡፡ /ኧ/ የመሀል አናባቢ ሲሆን፣ /ሰ/ ተናባቢ የድድ ድምፅ ነው፡፡ ድድም ከላንቃ ጋር ሲወዳደር ደረጃው ታቸኛነት ነው፡፡ ስለዚህም /ኧ/ ከ/ይ/ በፊት ሲገባ፣ የ/ይ/ን የላየኛነትና ፊተኛነት ባህሪያት ወስዶ [ኤ] ይሆናል፡፡ እንደዚሁም /ሰ/ የላየኛነቱን ባህሪ ወስዶ [ሸ] ይሆናል፡፡ /ይ/ ሁለቱንም ባህሪያቱን ይሰጣል ማለት ነው፡፡ ላየኛነትን ለ/ሰ/ ፊተኛነትን ደግሞ ለ/ኧ/፡፡

የተገደፈው ድምፅ /ይ/ ለመሆኑ ማስረጃው ምንድን ነው ቢባል፣ መልሳችን እንደ /ኧ/ ያለ የመሀል አናባቢ ድምፅ ወደ [ኤ] ሊለወጥ የሚችለው ፊተኛ እና ላየኛ ከሆነ ድምፅ በፊት ሲገኝ ብቻ ነው፡ የሚል የሆናል፡፡ እነዚህን ባህሪያት የያዙ ድምፆች ደግሞ /ኢ/ እና /ይ/ ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ በተጠቀሱት ምሳሌዎች ውስጥ የተገደፈው ድምፅ /ኢ/ ሳይሆን /ይ/ ነው፡፡ /ኢ/ ቢሆን ኖሮ የ ሸጠ ታህታይ ቅርፅ /ሰኧኢጥኧ/ ይሆን ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችል አይደለም፤ ምክንያቱም ቋንቋዋ የአናባቢ ክትትሎሽን አይፈቅድም፡፡ ሁለተኛም የተገደፈው ድምፅ በርግጥ /ይ/ ለመሆኑ፣ የሸጠ ሰማዊ አቻ በሆነው ቃል፡ በሽያጭ ውስጥ [ይ] በግህድ መከሰትዋ ማረጋገጫ ነው፡፡

መሸ የሚለው ግስ ሁኔታም እንደ ሸጠ ነው፡፡ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት /ይ/ የምትገባበት ቦታ ነው፡፡ መሸ ውስጥ /ይ/ የምትገኘው በቃሉ መሀል ላይ ሳይሆን፣ በመድረሻው ነው፡፡ ለዚህም ነው በአርዕስታዊ አቻው፣ ማለትም በመምሸት ውስጥ [ት] በምትክነት የምትታየው፡፡

/ይ/ ከፍናቢ ድምፅ እንደሆነች ቀደም ሲል ስለ ድምፆች አፈጣጠር ስንወያይ ገልፀናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ባህሪውን ለጎረቤቱ እያጋባ በቃል መሀከል የሚጠፋው ሌላው ከፍናቢ /ው/ ነው፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን እንደ ጠረ

እና ዞረ ያሉ ግሶች ናቸው። እንደነዚህ ያሉ ቃላት ላዕላይ ቅርፆች ሁለት ተናባቢ ብቻ የሚታይባቸው ናቸው፡፡ ከአናባቢያቸው መካከልም የመጀመሪያው /እ/ ነው። እንደ ሰበረ እና እንደ ደመረ ያሉ ግሶችን ስንመለከት ግን በየተናባቢያቸው መካከል ላይ የሚገኘው ድምፅ /ኧ/ የሚለው አናባቢ እንደሆነ እንረዳለን። ይህ መደበኛው የግሶች ስርዓት ነው። የየግሱ አናባቢ ድምፅ ከ/ኧ/ የተለየ የሚሆነው፣ በግሱ ታህታይ ቅርፅ ውስጥ ከነበሩት ተናባቢዎች መካከል አንደኛው በላዕላይ ቅርፅ በማይታይበት ጊዜ ነው፡፡ ተናባቢዎቹ ድምፆች በሙሉ በላዕላይ ቅርፅ የሚታዩ ከሆነ፣ አናባቢው ድምፅ ምን ጊዜም /ኧ/ ነው።

ከዚህ አንፃር ሲታዩ፣ እንደ ጦረ ያሉ ግሶች አንድ ተናባቢ ድምፅ ጎድሎአቸዋል ለማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የመጀመሪያው አናባቢያቸው /ኧ/ መሆን ሲገባው፣ /እ/ ሆኖአልና፡፡ የማንኛውም መደበኛ ግሰ አናባቢ /ኧ/ ነው ካልን፣ የጦረ እና የዞረ ታህታይ ቅርፅም እንደሚከተለው መሆን አለበት፡፡

/ጥኧውውኧርኧ/ 12
/ዝኧውውኧርኧ/

በግልፅ እንደሚታየው፣ በሁለቱም ግሶች ውሰጥ ቅድመ-መድረሻው ተናባቢ /ው/ ነው፡፡ አናባቢውም /ኧ/ ነው፡፡ በታህታይ ቅርፁ ውስጥ /ው/ የሚለው ተናባቢ ለመኖሩ ሶስት ማስረጃዎች አሉ፡፡ አንደኛው ከፍ ሲል እንደተጠቆመው የመጀመሪያው ተናባቢ ድምፅ ከመሀለኛነት ወደ ሁዋለኛነት፣ ማለትም ከ/ኧ/ ወደ /እ/ መለወጡ፣ ሁለተኛው ራሱ /ው/ የግሶቹ ሰማዊ አቻዎች በሆኑት፣

ጥውር [ጥእውውእር] 13
ዘዋሪ [ዝኧውእርኢ]
መዘውር [ምኧ-ዝኧውውእር]

በሚሉት ቃላት ውስጥ በግሀድ መከሰቱ ሲሆን፣ ሶስተኛው የየቃሉ መነሻ ተናባቢ ከዘርግነት ወደ ከብነት መለወጡ ናቸው፡፡ የግሶቹን የመነሻ ተናባቢ ድምፅ ለውጥ ከሚከተለው የየግሶቹ ላዕላይ ቅርፅ መመልከት ይቻላል፡፡

ጦረ [ጥʷኦርኧ] 14
ዞረ [ዝʷኦርኧ]

በግልፅ እንደሚታየው፣ በየታህታይ ቅርፁ ውስጥ /ጥ/ እና /ዝ/ የነበሩት ድምፆች በየላዕላይ አቻቸው ውስጥ ወደ [ጥʷ] እና [ዝʷ] ተለውጠዋል፡፡

የየግሶቹ ታህታይ ቅርፅ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ከሆነ፣ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ /ው/ ባህሪውን ቀድሞት ለገባው አናባቢ ለ/ኧ/ ሰጥቶ ጠፍቶአል ማለት ነው፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ ጥያቄው፡ /ው/ ለ/ኧ/ የሰጠው ባህሪ ምንድን

በእዝባር ውስጥ የሚታዩት ደግሞ ተደራጊ ስሞች ይባላሉ፡፡ አንድ ድርጊት የተፈፀመበትን፣ ማለትም የድርጊት ተጠቂ የሆነውን ነገር፣ ያመለክታሉ፡፡ በ(ለ) የመጀመሪያ ረድፍ ውስጥ የሚታዩት፣ የውጤት ስሞች ይባላሉ፡፡ አንድ ድርጊት ከተፈፀመ በሁዋላ የሚታየውን ውጤት ወይም ድራጊ ነገር ያመለክታሉ፡፡ ተደራጊዎቹና ድራጊዎቹ ቅደመ-መድረሻ ድምፃቸውን ያጠብቃሉ፡፡ በዚህም ምንም ድምፅ ከማያጠብቁት ከአድራጊ ስሞች ይለያሉ፡፡ ተደራጊና ድራጊ ስሞች የሚለያዩት /ተ/ን በማስቀደምና ባለማስቀደም ብቻ ነው፡፡ ተደራጊዎቹ ብቻ /ተ/ን ያስቀድማሉ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታም የዚሁ የቅድመ-መድረሻ ድምፅ መጥበቅና አለመጥበቅ በግሶች መካከልም ልዩነትን ይፈጥራል፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| /ጥኧርርኧግኧ/ | ጠረገ | /ይ-ጥኧርግአአል/ | ይጠርጋል | 4 |
| /ጥኧርርኧብኧ/ | ጠረበ | /ይ-ጥኧርብአአል/ | ይጠርባል | |
| /ስኧብብኧርኧ/ | ሰበረ | /ይ-ስኧብርአአል/ | ይሰብራል | |

በመጀመሪያው ዕዝባር ውስጥ የተመለከቱት ግሶች የቀዳማይ አአንቀፅ ግሶች ይባላሉ፡፡ ያለቀ ድርጊትን ያመለክታሉ፡፡ በሶስተኛው ረድፍ የሚታዩት ደግሞ የካልዓይ አአንቀፅ ግሶች ይባላሉ፡፡ የሚያመለክቱት ያላለቀ ወይም ያልተጀመረ ድርጊትን ነው፡፡ የሁለቱን አአይነት ግሶች ቅድመ-መድረሻ ተናባቢ ድምፅ ብንመለከት፣ በቀዳማዮቹ ውስጥ ድምፁ እንደጠበቀ፣ በካልዓዮቹ ውስጥ ደግሞ እንዳልጠበቀ እንረዳለን፡፡ የሁለቱ አአንቀፆች ልዩነት መሰረት የዚህ ድምፅ መጥበቅ ወይም አለመጥበቅ ነው፡፡ ከዚህ አአንፃር ሲታይ፣ ጥብቀት ስሞችንና ግሶችን በአአይነት በአአይነት የመለያየት ተግባር እንዳለው እንረዳለን፡፡ ቅድመ-መድረሻው ድምፅ የሚጠብቀው፣ ቀደም ሲል ግድፈትን አአስመልክተን እንደገለፅነው፣ ስነ-ድምፀ-ልሳናዊ በሆነ ምክንያት ብቻ ሳይሆን፣ ስነ-ምዕላዳዊ በሆነ አአገባብም ጭምር ነው፡፡

ከዚህ ላይ ጥብቀት በቃል መነሻ ካልሆነ በስተቀር፣ በሌላ በማንኛውም ቦታ ሊከሰት ይችላል፡፡ በቃል መካከል ላይ የሚከሰተው ከላይ በተራ ቁጥር (3) የሚታየውን ይመስላል፡፡ በቃል መድረሻ የሚከሰተውን በሚከተሉት ምሳሌዎች እናሳያለን፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| /ስ-ብ-ረ-/ | [ስኧብኧርር-] | ሰበር- | 5 |
| /ፍ-ጥ-ን-/ | [ፍኧጥኧንን-] | ፈጠን- | |
| /ው-ስ-ድ-/ | [ውኧስኧድድ-] | ወሰድ- | |

ክትትሎሽ ሊከሰት ይችላል። ለምሳሌ፣ <u>ቀልድ</u> (ቅኽልድ) እና <u>ሰቅ</u> (ሰኽቅቅ) በሚሉት ባለ አአንድ ቀሰም ምዕላዶች መጨረሻ ላይ የሁለተኛ መደብ አመልካች የሆነውን /-ሀ/ን ብንጨምር፣ የምናገኘው <u>ቀልድሀ</u> /ቅኽልድ-ሀ/ እና <u>ሰቅሀ</u> /ሰኽቅቅ-ሀ/ የሚል ይሆናል። ይህም ከአናባቢው ቀጥሎ ሶስት ተናባቢዎች ተከታትለው እንደ ገቡ ያሳያል። ይህ ደግሞ ከቋንቋው የቀሰም አወቃቀር ሰርዓት ውጭ ነው። ምክንያቱም የአወቃቀሩ ሰርዓት ሶስት ጨራሽ ተናባቢዎችን አይፈቅድም። ሰርዓቱን እንዲከተል ከፈለግን፣ ከሁለተኛው ተናባቢ ቀጥሎ፣ አንድ አናባቢ ድምፅ ግልቃ ማስገባትና የተከታተሉትን ተናባቢ ድምፆች መለያየት ያስፈልጋል። የምናስገባው እናባቢም፣ ማንኛውም ሳይሆን /እ/ ብቻ ነው።

ይሀ አናባቢ በተጠቀሉት ቦታዎች ሲገባ፣ የምናገኘው <u>ቀልድሀ</u> [ቅኽልድእሀ] እና <u>ሰቅሀ</u> [ሰኽቅቅእሀ] የሚል ይሆናል። ሀገ-ወጥ የነበረው የሶስት ተናባቢዎች ክትትሉሽ፣ በገባው አናባቢ ምክንያት ህገኛ ሊሆን ችሉአል። በዚህ አይነት የተናባቢዎችን ክትትሉሽ ለማስቀረት የሚገባ አናባቢ *<u>ሰርጎ-ገብ</u>* አናባቢ ሲባል፣ የማስገባቱ ሂደት ደግሞ *<u>ሰርገት</u>* ይባላል።

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም ሰርጎ-ገብዋ አናባቢ በተናባቢዎቹ መካከል ስትገባ፣ በፊት የነበረው የቀለም አወቃቀር ይቀየራል ወይ? የሚል ነው። <u>ቀልድሀ</u> [ቅኽልድእሀ] የሚሰውን ቃል አንውሰድና ሁኔታውን አሰቲ እንመልከተው። ቃሉ ሁሰት ቀሰሞች አሉት። የመጀመሪያው ቀለም በፊትም /ኽ/ በሚሰው አናባቢ ምሰሶነት የተፈጠረውና ቀልድ [ቅኽልድ] የሚሰው ሲሆን፣ ሁሰተኛው ደግሞ ሰርጋ በገባችው አናባቢ አማካኝነት የተፈጠረው ሁሰተኛው ቀሰም ነው። አፈጣጠሩም እንደሚከተለው ነው።

(ሀ)  1

በያናባቢው አናት ላይ የሚታዩት ቋሚ መሰመሮች አናባቢዎቹ የቀለሙ ምሰሶ ወይም ቋሚ መሆናቸውን ያመለክታሉ። ቀደም ሲል ስለ ቀለም አወቃቀር ባየነው ሰርዓት መሰረት፣ እናባቢዎቹ መጀመሪያ በስተግራቸው ካለው አንድ ተናባቢ ጋር ይቀናጃሉ። ይህን ሲያደርጉ ቅንጅቱ የሚከተለውን ይመስላል።

(ለ)  2

ከዚህ በሁዋላ አያንዳንዱ አናባቢ በሰተቀኙ ካለው ተናባቢ ጋር እንደገና ይዋቀራል። ይህ ሲሆን፣ በ(ለ) የተመለከተው መዋቅር የሚከተለውን ይመሰላል።

(መ) 3




ቅኧልድእህ

በሰርጎ-ገብዋ አናባቢ ምክንያት ሁለት ቀለሞች ሊፈጠሩ ችለዋል፡፡

ሰርጎ-ገብዋ አናባቢ ከመግባትዋ በፊት የነበረው ቀለማዊ አወቃቀር የሚከተለውን ይመስል ነበር፡፡

ቀ 4



ቅ ኧ ል ድ

አሁን የዚህንና ከላይ በ(መ) የተመለከተውን የቀለም አወቃቀር እናነፃፅር፡፡ በዚህ ቀለም ውስጥ የጨራሹ ክፍል የሆነችው ተናባቢ ድምፅ፣ ማለትም [ድ]፣ በ(መ) ውስጥ ሰርጋ ከገባችው እናባቢ ጋር ተዋቅራ የሁሰተኛው ቀለም ከፋች ተናባቢ ሆናለች፡፡ ያወቃቀር ለውጥ አድርጋለች ማሰት ነው፡፡ ይህም ስለሆነ፣ የሁለቱ ቀለሞች ይዘት ከላይ እንደሚታየው [ቅኧል - ድእህ] የሚል ቅርፅ ሊይዝ ችሉአል፡፡ ሁለቱም ቀለሞች እኩል /ተአተ/ እና /ተአተ/ የሚል መዋቅር ሊይዙ ችለዋል፡፡ ባጭሩ /ተአተተ/ የነበረው መዋቅር፣ የመጨረሻ ተናባቢውን ለሁለተኛው ቀሰም ሰጥቶ፣ /ተእተ/ ሆኖአል፡፡ ስለዚህም ከላይ ለተነሳው ጥያቄ መልሳችን፣ አወን የአወቃቀር ለውጥ ሲኖር ይችላል የሚል ነው፡፡ ለውጡም ሁለት ጨራሽ ተናባቢ ያለው ቀለም፣ የመጨረሻውን ጨራሽ ተናባቢ ለሚቀጥለው ቀለም ከፋች ተናባቢ እንዲሆን የሚያስገድድ ነው፡፡ ባጭሩ ብዙ ጨራሽ ተናባቢ ያለው፣ ምንም ከፋች ተናባቢ ለሌለው ቀለም እንደሚሰጥ ያሳያል፡፡

ከተሰጡት ምሳሌዎች እንደምንረዳው፣ አናባቢዋ ሰርጋ የምትገባው፣ በቀለሙ መድረሻ እና ቅድመ-መድረሻ ተናባቢዎች መካከል ነው፡፡ ሰርገቱ ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም፡፡ በቃል መነሻ ላይ በሚገኙ ተከታታይ ተናባቢ ድምፆች መካከልም ሊካሄድ ይችላል፡፡ ለዚህ የሚከተሉት ምሳሌዎች ናቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| /ል-ብ-ስ/ | [ልእብሰ] | 5 |
| /ጥ-ብ-ቅ/ | [ጥእብቅ] | |
| /ው-ር-ስ/ | [ውእርሰ] | |

ርግማን ([ርእግምእን] ) የሚለውን ቅርፅ እናገኛለን፡፡ በሌላ በኩል፣ ይህችው አናባቢ ከመነሻው ተናባቢ፣ ማለትም ከ/ር/ ጋር ቦታ በመቀያየር በቃሉ መነሻ ላይ ስትገባ፣ [እርግምእን] የሚል ቅርፅ እናገኛለን፡፡ ይህ ቅርፅ ግን ከላይ ተጠቃሎ ከተቀመጠው ህግ ያፈነገጠ ነው፡፡ ምክንያቱም ከአናባቢው ቀጥሎ ሶስት ተከታታይ ተናባቢዎች ስለሚገኙበት ነው፡፡ በቃል መካከል ቋንቋዋው የሚፈቅደው የሁለት ተናባቢዎችን ክትትሎሽ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም የሶስቱን ተናባቢዎች ክትትሎሽ ለማስቀረት፣ ስርጉ-ገብዋን አናባቢ ከሁለቱ ተከታታይ ተናባቢዎች ቀጥሎ እንደገና ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሲሆን፣ እርግማን ([እርግእምእን]) የሚለውን ቅርፅ እናገኛለን፡፡ አናባቢው ሁለት ሂደቶችን እአልፎእአል ማለት ነው፡፡ አአንደኛው ከመነሻው ተናባቢ ቀጥሎ በሚገኙት ክፍት ቦታዎች መግባት ሲሆን፣ ሁለተኛው ከመነሻው ተናባቢ ጋር ቦታ ተቀያይሮ የቃሉ የመነሻ ድምፅ መሆን ነው፡፡

ይህ ከመነሻው ተናባቢ ድምፅ ጋር ቦታ የመቀያየር ሂደት ግን ውሱን ነው፡፡ አናባቢው ቦታ የሚቀይረው የቃሉ የመነሻ ተናባቢ እንደ /ር፣ ን ፣ ል/ እና /ስ/ ያለ ቀጣይ ድምፅ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ቀጣይ የሚባሉት ትንፋሽ ሳይቋረጥ የሚፈጠሩ ድምፆች ናቸው፡፡ እንደ /ክ፤ ድ፣ ግ፣ ወዘተ፤/ ካሉ ትንፋሽ ከሚቆርጡ ድምፆች ይለያሉ፡፡

በሌላ በኩል ግን ስርጉ-ገብዋ አናባቢ በሌሎች ተናባቢ ድምፆች በሚጀምሩ ቃላት መነሻ ላይም የምትገባ ትመስላለች፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| | | |
|---|---|---|
| እደላ | [እድድኸልእ] | 10 |
| እገዳ | [እግግእድእ] | |
| እቅድ | [እቅቅእድ] | |
| እከት | [እክክእት] | |

እንደነዚህ ያሉ ቃላት ታህታይ ቅርፅ የሚጀምረው /ዕ/ በሚለው ተናባቢ የማንቁርት ድምፅ ነው፡፡ ለዚህ ምልክቱ ግሱ /እ/ በሚለው አናባቢ መጀመሩ ነው፡፡ ይኸውም አደለ /አድድኸለኸ/፣ አገደ /አግግኸድኸ/፣ ወዘተ፣ ስንል ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ የአማርኛ ግስ ታህታይ ቅርፅ የሚጀምረው በጠቅላላው በተናባቢ ድምፅ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ስንነሳ፣ አደለ የሚለው ታህታይ ቅርፅም /ዕኸድድኸልኸ/ የሚል መሆን አለበት፡፡ ቀደም ሲል፤ ስለ ግድፈት ስንወያይ /ዕ፣ ው፣ ይ/ እና /ህ/ ባህሪያቸውን እጠገባቸው ለሚገኝ አናባቢ እያጋቡ እንደሚገደፉ ገልፀን ነበር፡፡ በዚሁ መሰረት /ዕ/ የታቸኛነት ባህሪዋን ከእሰዋ ቀጥሎ ለሚገኘው ለ/ኸ/ አጋብታ ተገድፋለች፡፡ /ኸ/ም በዚሁ ተጋቦት ምክንያት ወደ /እ/ ተለውጣለች፡፡ ይህ እንግዲህ በግሱ ቅርፅ ላይ የሚካሄድ ለውጥ ነው፡፡

ከላይ የሚታዩት ቃላት ግን ስሞች ናቸው፡፡ አፈጣጠራቸውም ከግስ አፈጣጠር የተለየ ነው፡፡ ለምሳሌ እደላ የሚለውን ብንወስድ /ዕ-ድድ-ል/ ከሚለው

መስረት ለበቅ እና በስቅ የሚሉትን ቅርፆች አወጣጥ እንደሚከተለው አሳይተን ጉዳዩን እንቋዋጨዋለን።

/ል$_1$ኧብ$_2$ኧቅ/ 7

[ል$_1$ኧብ$_2$ኧቅ] [ብ$_2$ኧል$_1$ኧቅ]

ታህታይ ቅርፁ በእዝባር የተመለከተው ነው። ከእሱ ላይ ሁለት ላዕላይ ቅርፆች ተመስርተዋል። የተመሰረቱትም የመጀመሪያዎቹን ሁለት ተናባቢዎች በታ በመቀያየር ወይም ባለመቀያየር ነው። የሚቀያይረው [ብ$_2$ኧል$_1$ኧቅ] የሚለው የገጠሩ ቀበልኛ ቃል ነው።

ይህን በዚህ እንተወውና በዚህ ክፍል እስካሁን በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው እናጠቃለው። በመሰረቱ ለማየት የሞከርነው ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮችን ነው። የመጀመሪያው በአማርኛ ውስጥ የሚገኙትን የንግግር ድምፆች መጠን፣ አይነትና አፈጣጠር መመርመር ሲሆን፣ ሁለተኛው የነዚህኑ ድምፆች አቀነጃጀትና ከዚህም ላይ የሚሰርፀውን የተለያየ ድምፀ-ልሳናዊ ሂደት መመልከት ነው።

የመጀመሪያውን በተመለከተ፣ ቋዋንቋዋው 30 ተናባቢዎችና ሰባት አናባቢዎች እንዳሉት አይተናል። ከተናባቢዎቹ መካከል 13ቱ አግድ፣ ሰባቱ ፍትግ፣ አራቱ ፍግድ፣ ሶስቱ ሰርናዊ፣ ሁለቱ ከፍናቢ እና ሁለቱ ደግሞ ጎናዊ ናቸው። ይህ አከፋፈል ከባህርየ ፍጥረታቸው አኳዋያ ነው። ከመካነ ፍትረታቸው አንፃር ሲታዩ ደግሞ፣ ስድስቱ ከናፍራዊ፣(ሰነፈራዊውን [ፍ]ን ጨምሮ)፣ ዘጠኙ ድዳዊ፣ ሰባቱ ዳላንቃዊ (ላንቃዊያኑን [ይ] እና [ኝ]ን ጨምሮ) ስድስቱ ትናጋዊ፣ ሁለቱ ደግሞ ማንቁርታዊ ናቸው።

እናባቢዎቹ ደግሞ ሰባት ሲሆኑ፣ እነሱም ምላስ ወደ ፊትና ወደ ሁዋላ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ አኳዋያ፣ የፊት፣ የመሀል እና የሁዋላ ተብለው፤ እንዲሁም ይኸው አካል ወደ ላይና ወደ ታች ከሚያደርገው እንቅስቃሴ አንፃር፣ ላየኛ፣ ልከኛና ታቸኛ ተብለው በሶስት እንደሚከፈሉ አይተናል።

ከ/ህ/ በለተቀር ተናባቢዎቹ በሙሉ ሊጠብቁ ይችላሉ። ጥብቀቱም የትርጉም ልዩነትና የሰዋሰዋዊ ባህሪ ለውጥን ሊያስከትል ይችላል። እንደ ገና [ግኧንኣ] እና ገና [ግኧንንኣ] ያሉት የትርጉም ለውጥ የሚከሰትባቸው ቃላት ሲሆኑ፣ እንደ [ግእድድኣይ]፣ [ጥእርርኣጊ] ወዘተ፣ ያሉት የድራጊ፣ ማለትም የውጤት ስሞች፣ እና የተገብሮ ስሞች ናቸው። ተገብሮነትን ወደፊት እናየዋለን።

የተናባቢዎቹን ስርጭ ለንመለከት፣ ከ/ኻ/ በስተቀር ማንኛውም ሌላ ተናባቢ ድምፅ በቃል መነሻ፣ መሀል ወይም መድረሻ ላይ ሊገባ ይችላል። /ኻ/

ብቻ በቃል መነሻ አይገኝም፡፡ ከአናባቢዎቹ መካከልም የመሀለኞቹ ብቻ በሁሉም ቦታ ሲገኙ፣ ዳረኞቹ በቃል መነሻ ብቻ አይገኙም፡፡

አቀነጃጀታቸውን ስንመለከት፣ ተናባቢ ድምፆች በቃል መነሻ ብቻ ተከታትለው አይመጡም፡፡ በሌላ ቦታም ቢሆን ከትትሎሹ ከሁለት ተናባቢዎች አይበልጥም፡፡ በልጦ ሲገኝ፣ ሶስተኛውን ተናባቢ ከሁለቱ ቀዳሚ ተናባቢዎች የሚለይ አናባቢ ድምፅ ሰርጎ ይገባል፡፡ ሁለተኛም ከሚከታተሉት ድምፆች የመጀመሪያው ልቅ መሆን አለበት፡፡ አናባቢ ድምፆች በላዕላይ ቅርፅ ተከታትለው አይገቡም፡፡ ከተከታተሉ አንድም ከሁለቱ አንደኛው ይገደፋል፣ ወይም ወደ ከፍናቢነት ይለወጣል፡፡ ወደ ከፍናቢነት የሚለወጡት የፊትና የሁዋላ አናባቢዎች ናቸው፡፡

በዚህ መሰረት አጠቃላዩ የቁዋንቁዋው ቀለም አወቃቀርም /ተ-አ-ተ/ የሚል ነው፡፡ በዚህ አይነት የሚዋቀሩ ቀለሞች እየተከታተሉ ሊገቡ፣ ከሚፈጠረው ንከኪ የተነሳ የአንዱ ድምፅ ባህሪ ወደ ሌላው ድምፅ የመጋባት ሂደት ሊከሰት ይችላል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚታዩት የመካነ ፍጥረት ባህሪያት ከናፍራዊነት፣ ላንቃዊነትና ትናጋዊነት ናቸው፡፡ ከባህሪየ ፍጥረት አኩዋያ ደግሞ ድምፀት፣ ኢድምፀት፣ ጥብቀት፣ ልለት፣ ማንቁርታዊነት ዋና ዋናዎቹ ሂደቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የድምፅ ግድፈት፣ ሰርገት ወይም ቦታ ቅየራ ሊከሰት እንደሚችል አይተናል፡፡

ድምፀ-ልሳናዊ ሂደቶቹ በምዕላድ ውስጥ፣ በምዕላድ ድንበር ወይም በቃል ድንበር ላይ ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ በዚህ ረገድ፣ ከፊል ላንቃዊነት በምዕላድ ውስጥ ሊከሰት፣ ሙሉ (ድ)ላንቃዊነትና ኢድምፀት በምዕላድ ድንበር ላይ እንደሚከሰቱ አይተናል፡፡ በዚህም ይህን ክፍል ተሰናብተን ወደሚቀጥለው እንሄዳለን፡፡

## መልመጃ

1. የምላስን ፊተኛ መሀለኛ እና ሁዋለኛ ክፍሎች መሰረት በማድረግ የአማርኛን ድምፆች በጠቅላላ በሶስት ክፍሎች ይመድቡ፡፡

2. <u>ካላገኘንባቸውስ</u> የሚለውን ቃል በፎኒማዊ ስርዓት ይፃፉና ፎኒሞቹን በባህርየ ፍጥረታቸው መሰረት ይከፋፍሉ፡፡

3. /ኸ/ እና /ኘ/ ፎኒም መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ጥንድ ጥንድ ቃላት ይፈልጉ፡፡

4. የሚከተሉትን ድምፆች መካነ-ፍጥረት ይግለፁ፡፡

[ ም፣ ፍ፣ ጥ፣ ት፣ ስ ፣ ሽ፣ ጅ፣ ኸ፣ ቅ]

5.

| | | |
|---|---|---|
| ጥ | → | ጭ |
| ት | | ች |
| ድ | | ጅ |
| ዝ | | ዥ |
| ስ | | ሽ |
| ን | | ኝ |

(ሀ) ከቀስቱ በፊት (በስተግራ) የሚታዩት ድምፆች ከቀስቱ በስተቀኝ ወደሚታዩት እቻ ድምፆች የሚለወጡበትን ሂደት ይግለፁ፡፡

(ለ) ለእያንዳንዱ ድምፅ ለውጥ ምሳሌ የሚሆን ቃል በፎኒማዊ አፃፃፍ ያሳዩ፡፡

6. ጣለ፣ ማለ፣ ላለ፣ ወዘተ፣ የሚሉት ቃላት ስላ፣ ሰላ፣ ጠሉ፣ ወዘተ፣ ከሚሉት ቃላት ጋር እንዴት እንደሚመሳሰሉና እንዴት እንደሚለያዩ ያስረዱ፡፡

7. በርታ፣ ስረታ፣ አበረታታ፣ ካላበረታታህ የሚሉትን ቃላት የቀለም እወቃቀር ስርዓት ያሳዩ፡፡

8. <u>ቀጤማ</u> እና <u>ቄጠማ</u> እንዲሁም <u>ሚስጥር</u> እና <u>ምስጢር</u> በትርጉም አንድ ናቸው፡፡ በቅርፅ ግን መጠነኛ ልዩነት ያሳያሉ፡፡ የልዩነታቸው ምክንያት ምን እንደሆነ ይግለፁ፡፡

9. /ፍ/ ፡ /እእ/ ፡ /ዝ/ ፡ /ክ/

(ሀ) እነዚህን ፎኒሞች በመጠቀም በአማርኛ የቀለም እወቃቀር ስርዓት መሰረት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቀለሞችን አሳይ፡፡

(ለ) ከቀለሞቹ መካከል በአንዱ ውስጥ /ዝ/ ወደ [ስ] ይለወጣል፡፡ የለውጡን ሂደትና አቅጣጫ ይግለፁ፡፡

10. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት በፎኒማዊ ስርዓት ይፃፉ፡፡

እንክብል፣ እበት፣ እጉዋት፣ ሙጫ፣ ቅቅል፣ መቸ

11. ጥበቀት የትርጉም ለውጥ እንዴት እንደሚያስከትል ጥንድ ጥንድ ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ፡፡